መግቢያ

ኡምና ጌራኒ፥ ከልደት እስከ ዕውቀት ያሳለፈችውን ሕይወትና የምንኩስና ኑሮዋን እንዴት እንደ ወጠነች፣ ከዚያም ከገጠሟት መሰናክሎች እጅግ ጥቂቱን በሁለተኛው መጽሐፍ አይተናል።

በሦስተኛው መጽሐፍ ደግሞ፥ ለፈጣሪአችን በሰጊድ ምስጋና እያቀረብን፤ በአጭር ሕይወቷ የሰጠችውን ሰፊ አገልግሎት እንጽፋለን። አንዳንዶች የሚደግፉት ብዙዎች የሚያጣጥሉት የነበረውን ምናኔ (የበረሻ ሕይወት)፥ በውስጣቸው በእውነት እንዲያንሰራራ አድርጋለች። እግዚአብሔር ከእርሷ ጋር አለና፥ ከእያንዳንዱ ከሚደርስባት ፈተና ታድጓታል። በመንፈስ ቅዱስ እየታገዘች በምትፈጽማቸው ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች፤ በአካባቢዋ ባሉት ዘንድ ታላቅ አክብሮትንና አድናቆትን ተለማምለች። በምታደርገው ነገር ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ መሪነት ስላለበት፥ ያሰበችው ሁሉ ተፈጽሞላታል። ለመልካም አገልግሎት ጸጋዋ እንደሚበዛላት ሁሉ፥ ስሕተት ከፈጸመችም ተግሳጿን ድንቅ በሆነ መንገድ ትቀበላለች። ለዚህ ማስረጃችን በመፍረድ ምክንያት የደረሰባት (የገጠማት) ቅጣት ነው።

የገዳሙ አስተዳዳሪ የመሆኗ ነገር በአባቶችና እናቶች የተተነበየ ሲሆን፥ እንዲሁም በራእይ በብዙ መንገድ ተገልጠላታል። ምንም እንኳን ምድራዊ ሕይወቷ አጭር ቢሆንም፤ በሰማያት ግን ዘለዓለማዊውንና እስከ የሌለው ሕይወት ባለቤት መሆኗን ተረድተናል። በገዳማዊ ሕይወቷ፥ የገዳሙን ውስጣዊና ውጫዊ ሥርዓት በሙሉ፤ በአዲስ ሥርዓት ለውጣ፥ ደካማ ጎኖቹን የሚያሻሽል መሠረት ጥላለች። ለዚህ መሠረታዊ ለውጥ መርሕ አድርጋ የወሰደችውን «ቀኖና ጳኩሚየስ» የተሰኘ የገዳማውያን ማኅበራዊ ሕይወት አመራር፤ ከእግዚአብሔር የተቀበለችው ጸጋ ነው። ከዚህ በፊት በገዳሙ የማይታወቀውን፤ በአቶችን በአንድ ዐይነትና በተመሳሳይ መንገድ በማደራጀት፥ አንድና ወጥ የሆነ የአገልግሎት ሥርዓት (መዋቅር) ዘርግታለች። እንዲሁም ቋሚ መንፈሳዊ ጉባኤያትን አዘጋጅታና አስተዋውቃ በሥራ ላይ አውላለች።

መነኮሳይያቱን አስተባብራ፤ ለገዳሙ አዲስ ቤተ መጻሕፍትና የእደ ጥበብ መሥሪያ ሕንፃ፣ ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ ሕንፃዎችንና አብያተ ክርስቲያናትንም አሳንፃለች። የውስጠቹ (መነኮሳይያቱ) የሚተዳደሩበትንና የውጪዎቹም (ተሳላሚዎች) የሚስተናገዱበትን ሥርዓት አዘጋጅታ በማቅረብ፤ በሥራ ላይ እንዲውል አድርጋለች። ከ፲፱፷፭-፲፱፸፬ ዓ.ም. ባሉት ጊዜያት ውስጥ፥ የተለያዩ ችግሮች ገጥመዋታል። እንዲሁም ሲዲ ክሬይር (Sidi Krair) በተባለ በሰሜን ዳርቻ በሚገኝ ቦታ ላይ፤ ስላስገደመችው የአ/ስ/ሴ/አ/ገ የምንለው የምናስነብበው አለ።

ይህ በእርሷ የተቀጣጠለ፤ የገዳማዊ ዕድገትና ሥርዓት ችቦ፤ በግብፅ ገዳማውያት ደናግል እንዲበዙ ታላቅ አስተዋጽኦ ከማበርከቱም በላይ፤ ምንኩስና በተናቀበት፣ ዓለማዊ ነገሮችን በስፋት የሚያንጸባርቅና መንፈሳዊ ሕይወቱ የላሸቀ ትውልድ በነገሠበት በዚህ ዘመን፤ ብዙ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን ደናግል፥ ወደ ገዳማዊው የመላእክት ሕይወት እንዲቀላቀሉ አድርጓቸዋል። የመነኮሳይያቱ በትምህርት ማደግም፥ የእርሷ ልፋት ውጤት ነው[1]።

ልዩና ታላቋ እናታችን፥ በሕንፃ ሥራ ላይ የነበራት ትኩረትና የበኣት መስፋፋት፤ በዚያው ልክ የወጣንያኑን ቊጥር ሊያበዛው የቻለው፥ ለግንባታ ሥራ ዕድገት ያላት (በተለይ ልዩ የሚያደርጋት) ጠንካራ ፍላጎት ነው። የመነኮሳይያቱ ማኅበር እየበዛ መሄዱም፥ ለተጨማሪ የበኣት ግንባታ ምክንያት ሆኗል። የዚህ የተጨማሪ ግንባታ ጥያቄ፤ ንብረትነቱ የገዳሙ ሆኖ፥ በአገልግሎት ላይ ያልዋለውን ቦታና፤ አሮጌ ሕንፃዎችን ሁሉ አፍርሶ በማደስ፤ ሊሆን ይችላል ተብሎ ታስቦ የማያውቀውን ጎላፊነት ወስዳ[2] ታላቅ አገልግሎት እስከመስጠት አድርሷታል። ከክይሮ ውጪ በሚገኘው ለምና ምርታማ በሆነ፤ አል-ካናትር አል-ኼርያ Al-Kanater Al-Khairia በተባለ ሥፍራ መሬት ገዝታ፥ የልማት ሥራ ሠርታለች።

በዚህ እንደ እሳት በሚቀጣጠል የአገልግሎት ሕይወቷ፥ ሥጋዊ ድካምን ሁሉ ተቋቊማ የግብርናውንም ሆነ የምሕንድስናውን ሥራ በትጋት ትከታተል ነበር። ከጽኑ መመሪያዊቿ አንዱ ደግሞ፥ የካይሮውን ገዳም በየጊዜው ችላ ሳትል ማሳደስና አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ማድረግ ነው። የምትፈጽማቸውን አገልግሎቶች ሁሉ በመንፈሳዊ መነጽር በማየት ስለምትዳኛቸው፤ ውጤቱ ሁሉ ተጨማሪ ሥራ የማይጠይቅና ተፈላጊነቱም የታመነበት ብቻ ነው። ለማኅበሩ የማያገለግል ምንም ዐይነት እንቅስቃሴ እንዲደረግ አትፈቅድም። ስለዚህ በማንኛውም መንገድ ቢሆን፤ ለማኅበሩ ቀጥተኛ ጥቅም የማይሰጥ ምንም ዐይነት ሥራ አይሠራም።

እናታችን ጌራኒ፥ በዚህ ሁሉ የሥራ ውጥረት ላይ ሆናም ቢሆን፤ ለሁሉ የቀረበችና በሁሉም ዘንድ የምትገኝ ናት። ከሁለቱ ፓትርያርኮች ጋር የነበራትና በሁሉ ዘንድ የሚታወቀው፤ ቀረቤታዋና መተሳሰቧም እንዲሁ ሳይወሳ የሚታለፍ አይደለም። ከኣቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ጋር ስለ ነበራት ቅርበት፤ በኣንደበቷ ስትናገር በመቅረፀ

---

[1] Pieternella van Doorn-Harder, Cont/ry Coptic Nuns (Columbia:Univ.of South Carolina, 1995), p.81.

[2] በ፷ኛው መ.ዓ. በተገደመውና በእርጌዋ ካይሮ በሚገኘው የኣቡ ሰይፊን ገዳም ውስጥ፥ በ፰ኛው መ/ዓ ፪ኛው ሚሥዓመት ላይ፥ ጥቂት ድህ ቤተሰብ፤ በገዳሙ ውስጥ በሚገኘውና ለገዳሙ አገልግሎት በማይሰጠው፤ እርጌ ሕንፃ ውስጥ ሰፍረው ነበር። ከጊዜ ብዛትም ቊጥራቸው እጅግ ጨመረ። በ፲፱፻፹ዎቹ አካባቢ፥ ጣማፍ ጌራኒ እርጌዎቹን ሕንፃዎች ለማደስና ባዶ የነበረውን ሥፍራ ተጠቅማ አዲስ ሕንፃ ለመሥራት ወሰነች። ይህ ውሳኔዋ ጌዎቹን ሕንፃዎች ለማደስና ባዶ የነበረውን ሥፍራ ተጠቅማ አዲስ ሕንፃ ለመሥራት ወሰነች። ይህ ውሳኔዋ እውን ይሆናል ብሎ ለማሰብ እጅግ ከባድ ነበር። ምክንያቱም ያንን ሁሉ በእርጌው ሕንፃ የሰፈረ ነዋሪ ወዴት መውሰድ፤ እንዴትስ ልቀቁ ማለት ይቻላል? ሆኖም በእግዚአብሔር እርዳታ፤ ለነዋሪዎቹ የተሻለና ጤናማ ቦታ ፈልጋ፤ ወደዚያ እንዲገቡ ለማድረግ ችላለች።

ድምፅ የተወሰደ መረጃ አለን። ከአቡነ ሲኑዳ ፫ኛ ጋርም እንዲሁ፤ በጥልቅ መንፈሳዊ ፍቅር የታሰረ ቀረቤታ ነበራቸው። በታመመች ጊዜ፥ አቡነ ሲኑዳ ወደ ምታስዳድረው ገዳም ሊጠይቃት ሲመጣ የሚሰማት ደስታ ገደብ የለውም። ደስታዋ ከሥጋዊ ድካሟና ከሕመሟ ስቃይ በላይ ሆኖ ይሰማታል፣ ትበረታለችም። ሥጋዊ አባቱን እንዳየ ሕፃን ልጅ ልቧ በደስታ ይዘላል። እርሱም እንዲሁ ለእርሷ ያለው ቅርበት፥ ጽኑና ፍጹም አባታዊ ነው።

ከጳጳሳት፣ ቀሳውስትና ምእመናን ጋር ያላት ቅርበትና ስሜትም፥ ከዚህ የተለየ አይደለም። ሁሉም በእርሷ ልብ ያላቸውን ቦታ ያውቁታል። ለእያንዳንዱ የራሱ የሆነ ድርሻ አለው። ከላይ እንደ ጠቀስነው፥ አሁንም ለኣንባቢያን ልናሳስብ የምንወደው፤ ይህ ቅዱስ የሆነ የሕይወት ታሪክ፤ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለትውልድ መተላለፍ ያለበት መሆኑን ነው። ከእግዚአብሔር የተሰጠንን በረከት ከእኛ ጋር በሓሴት እንዲቀምሱትና፥ ከፊታቸው የተደቀነውን የቤተ ክርስቲያን ፈተናና ታላቅ ኀላፊነት እንዲገነዘቡም ይረዳቸዋል። ስለ ቅዱሳን ሕይወትና ክብር፥ በእርሷ አማካይነት ለመመስከር፤ በዘመኑ የተገኘንና በዓይናችን ለማየት የበቃን ነንና።

ልዩ ታሪካችን የሆነውን፤ በኣሮጌዋ ካይሮ በሚገኘው ገዳማችን፤ በብፁዕ ወቅዱስ አባታችን አማካይነት የተፈጸመውን ሥርዓተ ምንኵስና ቀጥለን እናያለን። የኢሬንን ጥንካሬና ትጋት አጉልቶ ያወጣውን አጋጣሚም ሳናስነብብ አናልፍም። ይኸውም፥ ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን በግዞት ላይ በነበረ ጊዜ፤ ለቤተ ክርስቲያን ያደረገችው ታላቅ ድጋፍ ነው። በሥጋም በመንፈስም ትልቅ ሥራ ሠርታለች። ምንም እንኳን፥ እየሰጠች በነበረው አገልግሎት፤ የተለያዩ ማስጠንቀቂያዎችና ዛቻዎች የተሰነዘሩባት ቢሆንም እርሷ ግን እስረኞቹን ከማጽናናትና ከመርዳት የተቆጠበችበት ጊዜ አልነበረም።[3] ለቀሳውስቱም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ልጆች፤ የዕድሜና የደረጃ ልዩነት ሳታደርግ፥ ታሳይ የነበረውን አክብሮትና ፍቅር፥ በጥቂቱ አቅርበናል።

ሐኪም ቤት ተኝታ፤ የሕመሟ ደረጃ እጅግ በከፋበት ጊዜ እንኳን፥ እስከ መጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ዘለዓለማዊ እግዚአብሔርን ታመሰግን ነበር። በጸጋው ያከበራ ትን ፈጣሪዋን ለማወደስና ከእርሱ ጋር ለመኖር፥ ሰማዕት እንደምትሆንም ትናገር ነበር። ታማኙ ባርያ እናዳደረገው ሁሉ፥ በተሰጣት ጸጋ (መክሊት) አትርፋበት መቶ እጥፍ ለጌታዋ መልሳለች። የክብር አክሊሏንም ከቅዱሳን መላእክቱ ተቀብላለች። «አምስት መክሊት የተቀበለውም ቀረበና፦ አቤቱ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤

[3] በነሓሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፫፫ ዓ.ም. አቡነ ሲኑዳ ፫ኛ በግዞት ወደ ቅዱስ ብሶይ ገዳም ተልኮ ነበር። . . . ከእርሱ ጋርም፥ ስምንት ጳጳሳትና ሃያ አራት ቀሳውስት፣ እንዲሁም ሌሎች ስመ ጥር የሆኑ ቅብ ጦች ታስረዋል። በእርሱ ቦታ፥ አምስት ኮሚቴዎችን ያካተተ ቡድን ተተክቶ፤ አቡነ ሲኑዳም የቀድ ሞው ፓትርያርክ እየተባለ ነበር የሚጠራው። ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ወደ ካይሮ ተመልሶ መጥቶ በዓለ ልደትን ከዓሥር ሺህ በላይ ሕዝበ ክርስቲያን በተሰበሰበበት አክብሯል።

እነሆ ሌላ አም ስት አተረፍሁ ብሎ አምስት መክሊት አስረከበ። ጌታውም፥ መልካም፥ አንተ የታመንህ በጎ አገልጋይ በጥቂት የታመንህ ስለ ሆንህ በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው» (ማቴ.፳፭፥፳-፳፩)።

ነፍሷ፥ አፈር ከሆነ ሥጋዋ ከተለየችና በገነት ካረፈች በኋላ፥ እግዚአብሔር ክብሩን በእርሷ ይገልጥ ዘንድ፥ ስለ ምድራዊ ገድሏ፤ ብዙ ድንቆችን አድርጎላታል። ቅዱስ ሥጋዋ በሣጥን ውስጥ ሳለ፥ እንደ ፀሓይ ያበራ እንደ ነበር፥ በዙሪያዋ የነበረው ሕዝብ ሁሉ ተመልክቷል። አንድ ጳጳስም እግዚአብሔር ባናገረው፥ «በዚህ ሣጥን ውስጥ ሞት አይሸትም» ሲል ተደምጧል። በዕረፍቷ ምክንያት፤ ከዓለም ሀገራት የተሰበሰበው ሕዝብ ብዛትና፥ ቅዱስ ሥጋዋ ካረፈበት ሥፍራ የሚመጣው መልካም መዓዛ፤ እግዚአብሔር ለሚፈሩትና ለሚወዱት የሚሰጠውን እጋ ግልጽ አድርጎ የሚያሳይ ነው። «ዳግመኛም የክብሩን ባለጠግነት ሊያሳይ ቢወድ አስቀድሞ ለወደዳቸውና ለጠራቸው ለይቅርታ የተዘጋጁ የምሕረት መላእክትን ያመጣል» (ሮሜ.፱፳፫)።

ዕረፍቷ የሆነበት ዕለተ ረቡዕ፥ ጎዘናችን የከፋበት ዕለት ነበር። በጨፈገገው ንጋት እርሷን በሕይወት አላገኘናትም። የጋዝናችን ተካፋይ የሆነች ይመስል ፀሓይ ዋም አልወጣችም። ሰማዩ በደመና ተከልሎ ከቆየ በኋላ ያለውቅቱ ክባድ ዝናብ ዘነበ። በእናታችን ሕይወት ደስተኛ የነበረችው ተፈጥሮ እንኳን፥ በዕረፍቷ የእኛን ጎዘን ተጋርታለች። እማሆይ ኄራኒም ብትሆን፥ በውስጡ የፈጣሪዋን ሥራ ታያለችና፤ ተፈጥሮን ትወድ ነበር። የጸሎቷ በረከት በእኛም አድሮ ይኑር። አሜን።

አምና ጌራኒ፡ በመፍረድ ጎጢኣት የተቀበለችው ቅጣት፦

ማንኛውንም የቅድስና ምግባር በመለማመድና በራሷ ላይ በመፍረድ፤ ሁሌ በበኣቷ በእግዚአብሔር ፊት ለጸሎት ስትቆም፤ ራሷን እየከሰሰች ዕንባዋን ወደ እግዚአብሔር ታፈሳለች። ራስን መፈተሽና በበደሉት በደል ሁሉ መጸጸት፡ የሚሰጠውን የመንፈስ ነጻነትና ጥንካሬ፤ መማሪያ ይሆነን ዘንድ፤ እንደ ተለመደው ዘወትር ትነግረናለች። በዚህ መልኣካዊ ሕይወት ውስጥ እስካለን ወይም መኖር እስካለብን ድረስ፤ እርስ በራሳችን እንድንዋደድ፤ ትሑታን እንድንሆንና በማንም እንዳንፈርድ ትመክረናለች።

አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን እያስቀደስን ሳለን፤ ጥቂት መነኰሳይያት ስለ እጅ ሥራዎቻቸው ሲነጋገሩ ሰማኋቸው። ከቅዳሴ በኋላ፡ ወደ በኣቴ ስመለስ ደግሞ፤ ሌሎች ሁለት መነኰሳይያትም እንዲሁ ቆመው ሲነጋገሩ ሰማሁ። በውስጤ ምን ዐይነት ጠባይ ነው? ብዬ ለራሴ አሰብሁ፤ ተደነቅሁም። ለራሴ ሳስብ፡ «እየፈረድሁ» መሆኑን ግን አልተረዳሁትም ነበር። ከእነርሱ እንደራቅሁ ሁሉንም ረሳሁት። ማታ ከመተኛቴ በፊት፡ ራሴን እመረምር ዘንድ ለጸሎት ስቆም፡ ራሴን «ብዙ ድብቅ ድክመቶች አሉሽ። ሌሎች ምናልባት ደካማ ቢሆኑም የኣንቺን ያህል የበዛ ላይሆን ይች ላል»። ብዬ፡ ፈጣሪዬ መልካም የሆነውን መንገድ እንዲያመላክተኝ በጸሎት ጠየቅሁት።

ከመቅጽበት ራሴን በብረት በታጠረ ሰፊ ሕንፃ አጠገብ አገኘሁት። በሩ አጠገብ የነበረው ሰው ከፍቶ አስገባኝ። ቦታው እንደ ሞት የሚያስፈራ፤ ጨለማ የወረረውና መጥፎ ሽታ ያለው ነበር። ቤቱ በድንጋይ የተገነባ ሲሆን፡ ጕድጓድ ወይም ቀዳዳ በመሳሰሉ ክፍሎች ተከፋፍሏል። በእያንዳንዱ ቀዳዳ አንዳንድ መነኰሳይያት አሉበት። ሁሉም ያለቅሳሉ። ሽታውን ልቋቋመው አልቻልሁም፤ እንዲህ ዐይነት አስፈሪና አስ ከፊ ቦታ ምን ትሠራላችሁ? ስል ጠየቅኋቸው። እነርሱም የገዳማችንን ሥርዓት እናስ ታጕላለን፤ በእመምኔታችንም እንፈርዳለን፤ በእጎቶቻችንም እንዲሁ፤ ካሉኝ በኋላ፡ አን ቺስ ወደዚህ ምን አመጣሽ? ሲሉኝ፤ ዛሬ በመፍረድ ጎጢኣት ወድቄአለሁ አልኋቸው።

ከዚያ ቦታ ቶሎ መጥፋት ስለነበረብኝ፡ መውጫ ቀዳዳ መፈለግ ጀመርሁ። ወደ ገባሁበት በር የሚመራ መሰላል ነበረ። አጠገቡ ነጭ የለበሰ ሰው ቆሟል። ከዚህ ያስወጣኝ እንጂ የፈለገውን አሰጠዋለሁ ብዬ አሰብሁ። እርሱ ግን «እኔ የቦታው ጠባቂ ነኝ። ገንዘብም እልቀበልም» አለኝ። ምን ዐይነት አስጨናቂ ቦታ እንደሆነ ልብ ብለሃልን? ከዚህ በላይ እዚህ መቆየት አልችልም ስል መለስሁለት። እዚህ ያሉት ሰዎች ሁሉ በመፍረድ ጎጢኣት የወደቁ ናቸው። ከዚህ ጭራሽ አይወጡም። አንቺ ወደዚህ እንድትገቢ የተፈቀደልሽ ይህን እንድትመለከቺና ትምህርት እንድትወስጂ ነውና ልትጠነቀቂ ይገባሻል አለኝ። እሺ! በፈጸምሁት በደል ተጸጽቻለሁ። ሁለተኛም

በማንም ላይ አልፈርድም። አሁን ብቻ ከዚህ ልውጣ አልሁት። እሺ! ብሎ አሰወኝና ጠባብ መንገድ አሳየኝ። ከመንገዱ ጥበት የተነሣ፡ በጎን ካልሆነ አያስሄድም።

በዚህ መንገድ ለማለፍ፡ ወይ ፊቴ ወይ ጀርባዬ በግድግዳው መቧጠጡ (መቧጨሩ) አይቀርም። ሁለተኛው ያሳየኝ መንገድ ደግሞ፡ እጅግ ሰፊና ሁካታ የበዛበት፤ ብዙ መሪኖች ያሉበትና በጎይለኛ ብርሃን የደመቀ ነበር። በጠባቡ መንገድ ከሄድሽ ገዳምሽን ታገኚዋለሽ። በሰፊው ከሄድሽ ግን ትጠፊያለሽ አለኝ። በጠባቡ መንገድ እንደ ምሄድ ነገርሁት። ከዚያም ፊቴ ከሚቧጠጥብኝስ ጀርባዬ እንደ ፈለገ ይሁን ብዬ፡ ጀርባዬን ወደ ግድግዳው እያስጠጋሁና፡ ፊቴን ለመከላከል እየሞከርሁ፤ እጅግ ረጅም መንገድ ከሄድሁ በኋላ፡ በገዳማችን ዙሪያ ወዳሉት ሦስት አብያተ ክርስቲያናት የሚያስገባውን በር አገኘሁት[4]። ድሮ ወደ ገዳሙ የሚገባው[5] በምሥራቃዊው በር ነበር። ወደ በኣቴ ገባሁና፡ ተንበርክኬ «አቤቱ ጌታዬ ሆይ! በድያለሁና ይቅር በለኝ። በዚያ አስፈሪ ሥፍራ ስላልተውኸኝ አመሰግንሃለሁ። ጌታዬ ሆይ፡ እስካዬን ተቀበለኝ። ዳግ መኖም በማንም ላይ እንዳልፈርድና ማንንም እንዳልወቅስ አንተ አርዳኝ» ብዬ ጸለይሁ። ገዳማዊ ሕይወቴን እንደ አዲስ እንድጀምርና ከመፍረድ የራቅሁ እንድሆን ይረዳኝ ዘንድ ተማጸንሁት።

ወደ ራሴ ስመለስ (ስነቃ)፡ ጸሎት በማደርስበት ቦታ ጥግ ላይ ነበርሁ። ከእግሮቼ በታች መሬቱ በዕንባዬ ርሷል። ያ አስጸያፊና መጥፎ ሽታ፡ አሁንም አፍንጫዬ ላይ አለ። ስለ ጎጢኣቴ፡ ሌሊቱን ሙሉ በዕንባ እየታጠብሁና ራሴን እየወቀሰሁ ስጸልይ ነጋ። በማግስቱ፡ ጀርባዬንና ትከሻዬን ሲያመኝና ጎንበስ ቀና ማለትም ከልክሎኝ ዋለ። ለእማሆይ ማርታ ሳሳያት፡ ጀርባዬ በሙሉ እንደተፋፋቀና ልብሴም በደም እንደተበላሸ ነገረችኝ። ቁስሉ ላይ ጸረ ባክቴርያ መድኃኒት ቀባችልኝ። ይህ ቁስልና የድካሜ ብዛት፡ ለሦስት ቀናት የሙቀት መጠኔን አርባ ዲግሪ ሴንቲግሬድ አድርሶት ከረመ። ከነበርኹበት ቦታ አስከፊነትና አስፈሪነት የተነሣ፡ በመደናገጤ፤ እንዲሁም ከዚያ ለመውጣት አደርግ በነበረው ጥረት፡ የደረሰብኝ ድካም ቶሎ አልተወኝም።

መነኰሳይያቱ በሙሉ፡ ከልክ በላይ መድከሜን በማስተዋላቸው፡ ምን ሆና ነው? እያሉ ሲያዩኝ፡ በበደሌ ምክንያት የተቀበልሁት ቅጣት ነው አልኋቸው። የገዳማችን አበ ንስሐ እስከ መጣበት ሳምንታዊ ጉብኝት ድረስ፤ ለኣንድ ሳምንት በዚህ ሁኔታ ቆየሁ። ለአበ ንስሓዬ የሆነውን ሁሉ ስነግረው፡ «በሰው እንዳትፈርጂ፤ ገዳሙን እንዳታማርሪና መነኰሳይያቱንም ምንም እንዳትናገሪ፤ ገና ከጅምሩ ይህን የመሰለ ትምህርት የሰጠሽን አምላክሽን ልታመሰግኚው ይገባሻል» አለኝ።

---

[4] ገዳሙ ሦስት በሮች ያሉት ሲሆን፡ ስሜናዊው የገዳሙ ወና መግቢያ በር ነው። ምዕራባዊው ወደ አጸድ ያመራል። ምሥራቃዊው በር ደግሞ ወደ ሦስቱ አብያተ ክርስቲያናት፡ የኣቡ ሰይፊን፤ የሊቀ ካህናቱ ቅዱስ ሹኑዳ ዳምሻርያ ተብሎ የሚጠራው የድንግል ማርያም አብ.ክ. የሚያስገባው ነው።

[5] {«ገ» እና «ባ» ጠብቀው ይነበቡ።}

የመንፈሳዊ አባቴን ምክር ተቀብዬ፥ በመነኰሳይያቴ መካከልም ሆነ በእነርሱና በእመምኔታ መካከል የሚደረገውን ማንኛውንም የቃላት ልውውጥ እንዳልሰማ፤ ጆሮ ዎቼን በጥጥ መድፈን ጀመርሁ። ትኵረቴን በግል ጉዳዬ ላይ ብቻ አደረግሁ። የሥራ ምድቤ የትም ይሁን የት፤ ከበላቴ ወጥቼ ቀጥታ ወደዚያ አመራለሁ። በሌላ ዓለም የምኖር እስከመስል ድረስ፤ በዙሪያዬ የሚሆነውን ማንኛውንም ነገር መከታ ተል ተውሁ። ይህን ሂደትሥ የኑሮዬ መመሪያ አድርጌ በማጽናቴ፥ ነፍሷን ከቅዱሳኑ ጋር ያሳርፈውና፤ በልዩ ፍቅር ከምትወደኝና እኔም እንደዚያው ከምወዳት እመምኔ ታችን እማሆይ ኬርያ ጋርም በዚሁ ሁኔታ ቀጠልሁ። ትጠራኝና «እማሆይ! እንዲህ እንዲህ ዐይነት ነገር ታውቂያለሽን፤ ሰምተሻልን?» ስትለኝ፥ በትሕትና «ኣይ! ምንም አላውቅም፤ እባክሽ! ለማወቅም አልፈልግም» እላታለሁ።

ይህን ያልሁበትን ምክንያት ስለምታውቅና ስለተረዳችኝ በምሰጣት መልስ ቅር አይላትም። ስለ መነኰሳይያቴ፤ ለእርሷ ማቅረብ ያለብኝ መረጃ ካለም የምነግራት በጥበባዊ መንገድ ነው። አንዲት መነኵሲት ለኣንድ ጉዳይ ልታናግራት ወደ ጽ/ቤቱ ከመጣች፤ እኔ የውጎ መቅጃ ይዤ ውጎ ላመጣ እሄዳለሁ። ወይም የሚታጠብ ዕቃ ፈልጌ አጥባለሁ እንጂ እዚያው ተቀምጬ ንግግራቸውን አላዳምጥም። በዚህ መንገድ ከመፍረድ ኀጢኣት ራሴን ጠብቄ እንደ መጽሓፉ መኖር ጀመርሁ።

<u>የባቡር ጉዞ ወደ ሳዕሳይ ገብፅ</u>፦ ገዳም በገባሁ በሦስተኛው ዓመት፥ እናቴ አረፈች። ከቤት ከወጣሁ ጀምሮ፤ አባቴ በሥራ ጉዳይ ወደ ካይሮ ሲመጣ ይጠይቀኝ ነበር። እናቴን ግን ዳግም አላየኋትም። ወደ ገዳም ለመግባት በዝግጅት ላይ ሳለሁ የነገረችኝን ግን አስታውሳለሁ «ለምን ትንሽ አትታገሺም? ከዚች ዓለም ልለይ ሦስት ዓመት ብቻ ነው የቀረኝ» ብላኝ ነበር። እኔም «እግዚአብሔር ስለ ልጆችሽ ሲል፥ ዕድሜሽን ያርዝም ልሽ። እኔ ግን አንቺ በሕይወት እያለሽ ወደ ገዳም መግባት እፈልጋለሁ» አልኋት።

እማሆይ ኬርያ ዋስፍ፥ ወደ ቤተሰቦቼ ሄጀ አጽናናቸው ዘንድ አዘዘችኝ። ከእማሆይ ኬርያ እስክንድር ጋር፥ ከንጋቱ በዓሥር ሰዓት የሚነሣውን ባቡር ተሳፈርን። ቀድሞን ይሄድ የነበረ ባቡር ተገልብጦ፥ መንገድ ስለተዘጋ፥ አስዩት ከመድረሳችን በፊት፥ አንድ በኣንድ ከባቡሩ እንድንወርድ ሆነ። ሰዉ ሁሉ፥ ሌላ ቀደም ብሎ የተነሣ ባቡር ለመያዝ፤ አንዱ ባንዱ ላይ ተተረማመሰ። ጨለማው ድቅድቅ ያለ ነው። እኛም ባትሪም ሆነ ክብሪት አልያዝንም። ባቡሩ የቆመበት ቦታ ደግሞ ለመውረድ አመቺ ባለመሆኑ፥ ከባቡር ወርደን መሬት ለመቆም መዝለል ይጠበቅብን ነበር። ስለዚህ፥ እግዚአብሔር እንዲረዳን እየጸለይን፤ ሰዉ ቀለል እስኪል ድረስ፤ ከእማሆይ ኬርያ እስክንድር ጋር ቁጭ ብለን መጠበቅ ጀመርን።

በድንገት አንድ ሥርዓት አስከባሪ መጥቶ፤ ከፊት ለፊታችን ቆመ። ገጽታው የተረጋጋ፤ መንፈሳዊ፤ ሰላማዊና ደግ ሰው መሆኑን ይናገራል። ትሑት በሆነ አንደበት፥ «እናቶቼ! እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ነውና ምንም አያስፈራችሁ!» አለን።

እኛም «እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን!» ብለን መለስንለት። እኔን «ስትወርጂ እንድረዳሽ እጅሽን ስጪኝ» አለኝ። እጁን ከመስጠት ተቆጠብሁና፥ አመሰግንኩው ዘልዬ ወረድሁ። ቀጠለና እማሆይ ኬርያን ሲጠይቃት እርሷም አመሰግናለሁ! ብላው የእኔን እጅ ይዛ ወረደች።

ከዚህ ሰው ላይ፥ በጣም የሚያንጸባርቅና የሚያስደንቅ ብርሃን ወጥቶ፥ የባቡሩን መንገድ ከርቀት አጥለቀለቀው። እኔና እማሆይ ኬርያ ሌላውን ባቡር ለመያዝ ሰንሮጥ ደግሞ፥ «ባቡሩ እናንተ ሳትሳፈሩ አይንቀሳቀስምና ሰጋት አይግባችሁ» አለን። ወደ ባቡሩ ሰንገባ፥ በሰው ተጨናንቆ አገኘነው። አጠገባችን ያለ መቀመጫ ላይ ተቀምጠው የነበሩ ሁለት ፖሊሶች፥ ከእኛ ጋር የመጣውን ፖሊስ ሲያዩ ሰላምታ ሊሰጡት ብድግ አሉ። እርሱም «እነዚህ ሁለት መነኰሳይያት ደክሟቸዋልና ማረፊያ ቦታ ይሻሉ» አላቸው። ፖሊሶቹ «እሺ! ሁሉም እንደ ትእዛዝህ ይፈጸማል» ብለውት መቀመጫቸውን ለእኛ ለቀቁልን። እያመሰገንን ተቀመጥንና፥ የረዳንን ሰው ማንነቱን ይገልጽልን ዘንድ ጠየቅነው። ወደ ገዳማችን መጥቶ የሰማዕቱን በረከት ያገኘ ዘንድም ጋበዝነው። ፈገግ አለና «እኔ አቡ ሰይፊን ነኝ» ብሎን ተሰወረ። መቀመጫቸውን የለቀቁልን ፖሊሶችና በዙሪያችን ያሉት ሁሉ ይህን ሲሰሙ እጅግ ተደነቁ።

እማሆይ ኬርያ «እጁን ባለመያዝሽ ለጥፍተሻል። ቡራኬውን እናገኝ ነበር» አለችኝ። አብረውን ያሉት ሰዎች፥ የአቡ ሰይፊንን ማንነትና ታሪኩን እንድንነግራቸው ይጠይቁን ጀመር። እኛም እስከ ጉዞኣችን ፍጻሜ ድረስ፤ ስለ አቡ ሰይፊን የምናውቀውን ሁሉ ተረክንላቸው።

ምንም ዐይነት መከራና ስብራት፥ በሥጋም፤ በነፍስም፤ በመንፈስም ሲገጥመን፤ በገጹሕ ልብ ሆነን የጌታችንን እርዳታ ከጠየቅን፥ ቅዱሳኑንና ሰማዕታቱን ልኮ መረጋጋትን ይሰጠናል እንጂ ፈጽሞ አይተወንም። ሰላምን፤ የመንፈስ መረጋጋትን፤ ጥንካሬንና ጽናትን ይለግሰናል። ሰውን የሚወድ፤ ደግና መሓሪ አምላክ ነውና፥ የመንግሥቱም ወራሾች ያደርገናል። ስለገዛ ራሳችን ድኅነት ሲል፥ በፍቅሩና በቸርነት ሥራው ይስበናል። የሚያስመካንና የሚራራልን ያለ እርሱ ማንም የለንም። ያለ እርሱ ፍቅር ምኞትና ደስታም አናገኝም።

ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስና፥ እቤት እንደ ደረስን ጎዝጎተኞቹ በሙሉ በአንድነት፥ «ለእናቴ ሞት ምክንያት እኔ መሆኔን» ነገሩኝ። እኔም «እጎትና ወንድሞቼን የሙት ልጅ ያደረግኋቸው እኔ ነኝ ማለት ነው?» ሰል ፈጣሪዬን ጠየቅሁ።

ጣማፍ ኄራኒ በእናቷ ሞት አምርራ እያለቀሰች ነበር። አንድ ቀን አንድ ቅዱሳኑን የመሰለና ብርሃናዊ ሰው ተገለጠላትና እየደጋገመ የመጽሓፍ ቅዱስ ጥቅስ አነበበላት። በምንባቡ ግን ልትረጋጋም ሆነ ሰላም ሊሰማት አልቻለም። ማንነቱን ስትጠይ

ቀው «አበ ባሕታውያን አባ እንጦንስ ነኝ» አላት። ታድያ የክርስቶስ መገለጫ የሆ ነው ቅዱስ መስቀል እጅህ ላይ የታለ? ብላ ስታማትብበት ወዲያው ብን ብሎ ጠፋ።

ከእናቷ ሞት በኋላ፥ ከቤተሰቡ ጋር ለኣንድ ዓመት ቆየች። በነዚህ ጊዜያት ውስጥ ሚች እናቷን በየዕለቱ ታያት ነበር። ስለ ቤቱ አያያዝና ስለሚገጥማት ማንኛ ውም ችግር፤ ጀኔፍየፍ እየመጣች ታማክራታለች። ከዓመት ቆይታ በኋላ፥ ወደ ገዳም እንደተመለሰች፥ የሆነውን ሁሉ ስትነግረን፥ መንግሥተ ሰማያት ለእርሷ ምን ያህል ቅርቧ እንደ ሆነ እናስባለን። እንደ ሕጉና በፍቅሩ ለሚኖሩት ሁሉ፤ የተዘጋጀላ ቸው ሥፍራ እንዳላቸውና፥ ፍጹማኑ ከፈጣሪያቸው ጋር ያላቸውን የጠበቀ አንድ ነት፣ በሥጋ ሞት የተለዩን ቤተሰቦቻችንም ሆኑ ወዳጆቻችን፥ ስለ እኛ እንደሚያስቡና እንደሚያዩን እናይባታለን። እንማርባታለን።

ለምሳሌ ከጣማፍ ታናናሽ እኅቶች አንዷ ከኃዘኗ መጽናናት ባለመቻሏ አብዝታ ታለቅስ ነበር። እናቷ ጀኔፍየፍ መጥታ ጠበል አጠጣቻት። ትንሿ ልጅም ከዕንቅልፏ የነቃችው ደስተኛና ኀዘኗን የረሳች ሆና ነው። ሌላ እኅቷም ታማ ነበር። ማታ ማታ ጀኔፍየፍ እየመጣች ብርድ ልብሷን ታስተካክልላትና ጸሎት ታደርስላታለች። በኣንድ የብርድ ወቅት ደግሞ፥ የትንሹ ወንድሟ ብርድ ልብስ ተንሸራቶ ወድቆ ነበር። ጀኔፍ የፍ መጥታ፥ አነሣችና አስተካክላ አለበሰችው። እርሱም ጠዋት ሲነሣ፥ ሌሊት በጣም በርዶኝ ነበር። እናቴ መጥታ አለበሰችኝና ሞቀኝ አላቸው።

ራሷ ጣማፍም ከኃዘኗ መጽናናት የቻለችው፥ እናቷ ያለችበትን ቦታ እግዚአብ ሔር ከገለጠላት በኋላ ነው። ታሪኩንም እንዲህ ስትል ነግራናለች፦ አንድ ቀን የእግዚአብሔር መላእክት፤ መምህራችን ቅዱስ ጳውሎስ የገለጸው ዐይነት፤ *ዐይን አይቶት ወደማያውቀው ድንቅ ሥፍራ* ወሰደኝ። ያየሁትን በቃላት ልንገራችሁ ብል፥ የእኔ ዕውቀት አይበቃውም። እናቴን ከኣንዲት ሴት ጋር ሆና አየኋት። እናቴም «መነኵሲት ናት ያልሁሽ ልጀ እርሷ ናት» ብላ ለሴትየዋ ነገረቻት። ከእናቴ ጋር በሥፍራው ስንዘዋወር፥ አረንጓዴ መስክ፤ የወንዝ ጅረት የሚመስል ውኃ፤ ውብ አበ ቦችና ልብን በፍጹም ደስታ ደስ የሚያሰኝ የብርሃን ድምቀት አየሁ። በገነት ውስጥ እግዚአብሔርን ያዩት እንደ ሆነ ስጠይቃት «አዎን! እናየዋለን። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው። ከእርሱ ጋር በመሆናችንም ደስተኞች ነን። እርሱ በሁሉም ቦታ አለ። የሌ ለበት ቦታም የለም» አለችኝ። ጣማፍ፥ በቆይታዋ ቤተሰቧን አጽናንታ ካረጋጋችና፤ ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆኑን ካረጋገጠች በኋላ፥ ወደ ገዳሟ ተመለሰች።

ምዕራፍ ሁለት

ሰማያዊ አዋጅ፥ የኅመራርና የኃላፊነት መክሊት።

ጣማፍ ኄራኒ፥ ገዳም ከገባችበት ከመጀመሪያዎቹ ቀናት ጀምሮ፤ ስለ መልካም ነቷና ቅድስናዋ፥ የነፍሷ ጠባቂዎችና መሪዎች ቅዱሳን መላእክት ስለ መሆናቸው፤ በብዙ ሰማያዊ ምልክቶች ተገልጠዋል። የነፍስ ድኅነት የሚሹትን ብዙዎችን እየረዱና እየመከሩ የመምራት፤ መልኣካዊ ሕይወትንም የማስተዋወቅ መክሊት ለመቀበል፥ በእግዚአብሔር ዘንድ የታመነችና የበቃች መለኮታዊ ክብርንም የተጎናጸፈች እናት ሆና ተገኝታለች። በዚህ የመንፈሳዊ አገልግሎት ጉዞዋ፥ በመንፈስ ቅዱስ እየተመ ራች፤ እግዚአብሔር ሞገስ ሆኗት፥ በጸጋ ላይ ጸጋን፤ በክብር ላይ ክብርን እያበዛላት ታይታለች። ውዷ እናታችን ጣማፍ፥ ገዳማዊ ሕይወቷን፥ በፍጹም ትኵረትና በታማ ኝነት ነበር የኖረችው። በልቧ ያሰበችውን ማንኛውንም ነገር ለኣባ ንስሓዋ ወይም ለእ መምኔቷ ታማክራለች። ምክራቸውንም በቅን ልቡና ተቀብላ፥ ሁሉንም እንደታዘዘ ችው ወይም እንደተመከረችው ብቻ ትፈጽማለች።

እንዲሁም፥ ከመጽሓፍ ቅዱስና ከኣበው ታሪክ ምንባባት፥ ብዙ ትምህርት ቀስማ ለች። ለእርሷ፥ ቅዱሳት መጻሕፍት ማለት፤ እንደ ፈለገች እየተጎነጨች ጥሟን የም ታረካበትና ነገረ እግዚአብሔርን የምታውቅበት፤ የምንጭ ውኃ ናቸው። እግዚአብሔር የለገሳት የማንበብን ፍቅር ብቻ ሳይሆን፥ በጥልቀት የመረዳትን፤ በልብ የመያዝና ያንን የያዘችውን ደግሞ እየመነዘረች (ከሕይወቷ ጋር እያናበበች) የመተግበርን ልዩ ጸጋም ነው። ከሌሎች መነኰሳይያት ይልቅ፥ የእርሷ መንፈሳዊ ዕድገት በግልጽ የሚታ የውና መልካም ፍሬ የሚያፈራውም ለዚህ ነው። ይህ ጸጋዋ የማስተዳደርና በፍቅር የመምራት ኀላፊነት የሆነውን ተጨማሪ ጸጋ «መክሊት» እንድትቀበል አብቅቷ ታል። ስለምትቀበላቸው ሰማያዊ መልእክቶችና ትምህርቶች፥ ወደዚያ ለመድረስም የሚገጥሟትን መሰናክሎች ሁሉ እንማርባቸው ዘንድ ትነግረናለች። እኛም ከምናየ ውና ከምትነግረን በመነሣት፤ መክሊቶቿ በሙሉ ፍጹም ሰማያዊ መሆናቸውን እንረዳለን።

የአማሆይ ኤፍሮዚና ትንቢት፦ *አማሆይ* ኤፍሮዚና (Ephrosena) *ያኔ* ከነበሩት መነኰሳይ ያት አንዷ ነች። በትውልድ ኢትዮጵያዊት ስትሆን፥ በስደት ወደ ግብፅ መጥታ፥ በዶ.ር ሙኒር ኔማጥኣላህ ቤት ታገለግል ነበር። የቤተሰቡ አባላትም ከእነርሱ እንደ አንዷ ያዩዋታል። ወደ ምንኵሰና ሕይወት ከገባች በኋላ፥ ለማንም አስቸጋሪና ከባድ የሆነውን ሥራ መርጣ ስትሠራ፥ ለራሷ ምንም ርኅራኄ አልነበራትም። ብዙ ጊዜ፥ *ግለሰብ ቤት አገለግል ከነበር፤ ለቤተ እግዚአብሔርማ ምንኛ አብዝቼ ማገልገል ይጠበ ቅብኝ ይሆን?!* ስትል ትደመጣለች። የምትሠራቸው አስቸጋሪና ጉልበት የሚጠይቁ ሥራዎች፥ ዕድሜዋን የሚመጥኑ አይደሉም። ያም ሆኖ እግዚአብሔር ጉልበቷን እን ዲያጠነክርላት እየተማጸነች፥ ያለ ዕረፍት ትሠራለች። ቀን ሙሉ አገልግሎት ስትሰጥ

ትውልና፣ ሌሊቱን ሙሉ ደግሞ በጸሎት ታሳልፋለች። የእርሷ የምንኩስና ሥርዓት እንደ በረሓውያኑና ባሕታውያኑ ነው። ሥጋም ሆነ አትክልትና ፍራፍሬ አትመገብም። በጾምም ሆነ ከጾም ውጭ፤ ምግቧ ሐለዋ Halva (ከሱፍ የሚሠራ ጣፋጭ)፥ ወይም ጀሊ (ከስኳርና ሎሚ የሚሠራ የረጋ መረቅ) ብቻ ነው።

ጸላኢ በጣም ይፈታተናት ነበር። በኣቷ ከእኔ (ጣማፍ) በኣት ፊት ለፊት ስለ ነበር፥ በበኣቷ ውስጥ የሚፈጸመው ሁሉ ይታየኛል። የውኃ ገንቦ ማንም ሰው ሳይ ዘው በኣየር ላይ ሲንቀሳቀስ አያለሁ። ከዚያ፥ ልክ ሰው እንደ ወረወረው ቢጤ፥ በመስ ኮታ ተወርውሮ ገብቶ፥ ፊቷን ይመታታል። ከዚያ «አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ በኃይ ልህ ድረስልኝ! ወዳጀ አቡ ሰይፊን ፈጥነህ ናልኝ!» ስትል እሰማታለሁ። እያለቀሰች ገድሏን ትቀጥላለች እንጂ አትረታለትም። ጥቂት ቆይቶ ደግሞ በኣቷ በብርሃን ጸዳል ይሞላል። እርሷም «የተረገማችሁ ሁሉ! ሸሻችሁ አይደል? ከኃይለ እግዚአብሔር ሸሻችሁ!» ትላለች። ከዚያ ለሁሉም በሚሰማ ድምፅ «እግዚአብሔር ቸር ነውና እግዚ አብሔርን አመስግኑት! ለሰሙም ዘምሩ መልካም ነውና! አክብሩት! አግኑት . . . ቸር ነቱ ለዘለዓለም ነውና» እያለች ውዳሴዋን በዝማሬ ታቀርባለች። ዝማሬዋን ስታበቃ ሌሊቱን በጸሎት ታሳልፋለች። እኔም ለእግዚአብሔር የምታቀርበውን ውዳሴና ዝማሬ ማድመጥ በጣም ያስደስተኝ ነበር። ጠዋት ሁላችንም ከየበኣታችን ስንወጣ፥ የደረሰ ባት ጉዳት ፊቷ ላይ ለሁሉም ግልጽ ሆኖ ይታያል።

ገና ወደዚህ ገዳም እንደገባሁና የወጣንያኑን ልብስ እንደ ለበስሁ፥ የእርሷን ቡራኬ አገኝ ዘንድ እማሆይ ኬርያ እስክንድር ይዛኝ ሄደች። የበኣቷ በር ሲንኳኳ፥ ከፈተችውና እማሆይ ኬርያን ብቻ አስገባቻት። በሯ አጠገብ ብቀምም፥ እንዳላየችኝ አሰብሁ። ወዲያው ደግሞ ጠራችኝና «ወጣኒቷ! ነይ ግቢና እዚህጋ ተቀመጪ። የኣሰ ተዳደር ሥራው የኣንቺ ይሆናል። በገዳሙ በኃላፊነት ትሾሚያለሽ» አለችኝ።

ከዚያ ወደ እማሆይ ኬርያ ዘወር ብላ፤ «እማሆይ! ልብ በይ! ይህች ልጃገረድ የገዳሙን ኀላፊነት ትረከባለች» አለቻት። እማሆይ ኬርያም፥ «እንዴ? እንኳን የገ ዳሙ ሰዎች ይቅሩና፥ ገና አይጡቹ እንኳን አላዩዋትምኮ» ስትላት፤ እናት ኤፍሮዚና «አይጥም አያት፣ ሰውም አያት፥ ልዩነት የለውም። እየነገርሁሽ ያለሁት አስተዳዳሪአ ችሁ እንደምትሆን ነው» አለቻት። እኔ ለተናገረችው ነገር ምንም ቦታ አልሰጠሁ ትም። ላስበውም አልፈለግሁም። ምንም እንኳን፥ ስለ ቅድስናዋ ብረዳም፥ ለራሴ ግን «ከኣሁን በፊት አይታኝ አታውቅም። በዚያ ላይ፥ ደካማ ኣሮጊት ናት» አልሁ።

<u>የኣባ ሚናስ አል ባራሙሲ (የኋላው አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ) ትንቢት</u>፦ ጣማፍ ጌራኒ ገዳም ከገ ባች ከጥቂት ወራት በኋላ፣ ጎይለኛ ራስ ምታትና የዓይን ሕመም ያውካት ነበር። እማሆይ ኬርያ እስክንድር ወደ ተለያዩ የኣንገት በላይ ሐኪሞች ዘንድ ብትወስዳ ትም፥ ምንም መፍትሔ ባለመገኘቱ፥ ይጸልይላት ዘንድ በኣሮጌዋ ካይሮ (በኣል

ጣሁና)[6] ይኖር ወደ ነበረው፥ ባሕታዊ አባ ሚናስ አል ባራሙሲ በእማሆይ ኬርያ ዋስትና ትእዛዝ ይዛት (ጌራኒን) ሄደች።

አባ ሚናስ አል ባራሙሲ፥ መስቀሉን ራሴ ላይ አኑሮና እጆቹን ጭኖ፤ ለረ ዥም ሰዓት ጸለየልኝ። ከዚያም ለእማሆይ ኬርያ «ይቺ ልጅ ማንበብ ታበዛለች። ሌሊ ቱንም ሳትተኛ ነው የምታሳልፈው። ጸላኢ ደግሞ ይህ ድርጊቷ እያንገበገበው ነው። ራስ ምታቱም የእርሱ የጦር አዋጅ ነው። እማሆይ! ለማየት ያብቃሽ እመምኔታ ችሁ ትሆናለች። በእርሷ የሥልጣን ዘመን፤ ብዙ ታላላቅ ሥራዎች ይሠራሉ። በገ ዳሙ አብያተ ክርስቲያናትን ታሳንፃለች። የመነኮሳይያቱም ቍጥር በእጅጉ ይጨም ራል» አላት። እማሆይ ኬርያም «አባቴ! ምን እያሉ ነው?» ስትለው፥ «እስከዚያ በሥጋ ከቆየሁ፤ አሁን ያልሁሽን ነገር እኔ ራሴ አስታውሰዋለሁ። ወደ ላይኛው ቤት ከሄድሁ ግን፥ የነገርሁሽን እንዳትረሺ» አላት። እርሷም «እግዚአብሔር ለእኛ ሊል ዕድሜና ጤና ይስጥዎ» ብላው ወደ ገዳማችን ተመለስን።

<u>ሠለስቱ መቃርስ</u>፦ ስለ ሰማያዊው አዋጅ ደግሞ እንዲህ ስትል ነገረችን፥ አንድ ሌሊት ሦስት ብርሃናውያን አባቶችን በሕልሜ አየሁ። ደረታቸው ላይ መስቀል አለ፤ በእጃ ቸውም ይዘዋል። አንድ ወንበር አምጥተው መጠኑን ይለኩ ጀመር። «ምንድር ነው የምትሠሩት?» ስላቸው፥ «በኣንቺ ልክ የሚሆን ወንበር እየሠራንልሽ ነው። ልኩን የምንወስደው፥ በተገቢው ሁኔታ እንከን የሌለው ሥራ ለመሥራት እንችል ዘንድ ነው» አሉኝ። እናንተ እነማን ናችሁ? ስላቸው፥ «እኛ ሦስቱ መቃርሶች ነን» አሉኝ። ስለ ሕልሜ ምንም የተረዳሁት ነገር ባለመኖሩ፥ ለንስሐ አባቴ ስነግረው፥ «ምንም ትኩረት አትስጪው» አለኝ።

በእርግጥም፥ ስለ እነርሱም ሆነ ስለ ተናገሩት ነገር ለማሰብ ጊዜ አላገኘሁም። ቄራሽ ረሳኋቸው። አንድ ሌሊት ግን፥ ከሕልም ይልቅ ወደ ራእይ ያመዘነ ነገር ገጠ መኝ። በራእዩ እጅግ ስለ ተደነቅሁ፥ ወዲያውኑ ረዷ ወደ ነበርሁት እማሆይ ኬርያ ዋስፍ በኣት ሄድሁ። የዚያን ሰሞን ታማ ተኝታ ስለ ነበር፥ ሌሊት ወደ በኣቷ እየሄ ድሁ የጤንነቷን ሁኔታ የማየትና፥ የምትፈልገውን ነገር የመጠየቅ ኀላፊነት ነበረብ ኝና፤ ዞሮ ዞሮ በሌሊት ወደ እርሷ መሄዴ አይቀርም ነበር። «እማሆይ! ሙሉ ለሙሉ ሳልተኛም ሳልነቃም፥ እያለሁ ራእይ ታየኝ» አልኋት። እዚህ በኣንቺ በኣት ውስጥ ያለሁ ይመስለኛል። ከዚያ የመነኮሳት ልብስ የለበሱ ሦስት አረጋውያን መጡ። ገጻ ቸው በጣም ያበራል። አንገታቸው ላይ መስቀል አለ፤ በእጃቸውም ይዘዋል። አንቺም በቀኝ እጅሽ በውስጡ ማብሪያ ክር ያለበት ፋናስ ይዘሽ ቆመሻል። ፋናሱን ከእጅሽ ተቀበሉና ለእኔ አስያዙኝ»።

[6] {ስለ አል-ጣሁና ታሪክ፡ ዝከረ ቅዱሳን ዘተዋሕዶ ፪ኛ መጽ. ፩፲፭፬ ዓ.ም / እ.አ/ ገጽ ፵፯ ላይ ይገኛል።}

ፍጥነትና ሁኔታ የገዳሙን ዋና በር፣ የቤተ ክርስቲያንን በር፣ የመጋዘኑንና ሌሎች ንም ቁልፎች በአንድነት የያዘው ሰንሰለት፣ ከእጀ ላይ ተነጠቀ። ወደ እማሆይ ኬርያ እስክንድር ሮጡ ሄድሁና «እርዳታሽን አፈልጋለሁ። ቁልፎቹ ከእጀ ላይ ተወሰዱ ብኝ» አልኋት። እርሷም «ተወሰደብኝ ማለት ምን ማለት ነው? እስቲ እንፈልገው» አለችኝ። ሁሉም ቦታ ፈልጌዋለሁ። ላገኘው ግን አልቻልሁም አልኋት።

ሐናዊ አስጠርታ ቁልፎቹን እንድናስቀይር ስጠይቃት፣ አሁን ሠራተኛ ለማም ጣት በጣም መሸቷል። ካለችኝ ብኋላ፥ በተረጋጋ መንፈስ «ጌራኒ! ነይ እስቲ፥ እውነ ቱን ንገሪኝ! በአንቺና በሰማዕቱ መካከል የተፈጠረው ምንድር ነው?» አለችኝ። «አል ወድህም! አንተንም ገዳምህንም አልፈልግም፥ ነው ያልሁት» ስላት፣ ደንግጣ ምን አልሽ? በይ አሁን፦ ፍጠኚና ይቅር እንዲልሽ ጸልዩ አለችኝ። እኔም «እውነቱን እስከ ተናገርሁ ድረስ ለምን ያዘንብኛል? በትክክል የሚሰማኝን ነው የተናገርሁት። በዚህ ንግግሬ፥ ምንም ስሕተት ያለ አይመስለኝም»። አያልኋት ሳለሁ፥ ድንግት ሐሳቤ ሁሉ ተቀየረና ትልቅ ስሕተት መፈጸሜን ተረዳሁ። የወራዳነት ስሜትም ተሰማኝ። ራሴን እየገሰጽሁና እየወቀስሁ ማልቀስ ጀመርሁ። «እንዴት እንዲህ አደርጋለሁ? ታላቁን ለማዕት እንዴት እንዲህ እናገረዋለሁ?» ብዬ እየሰገድሁ «በደል ፈጽሜአለሁ። ታላቁ የጌታዬ ሰማዕት ይቅር በለኝ!» ብዬ አምርሬ ማልቀስ ቀጠልሁ። እማሆይ ኬርያም «የጸጸት ለቅሶ በማልቀስሽ መልካም አድርገሻል። ነይ አሁን ዐረፍ በይ» አለችኝ።

ድግፍ አድርጋ ሶፋው ላይ ከጎኗ ዐሳረፈችኝ። ገና ስንቀመጥ፥ ሰውነታችን እስ ኪንቀጠቀጥ ድረስ፥ ክፍሉ እጅግ መልካም መዓዛ ባለው የዕጣን ሽታ ታወደ። ወዲ ያው ደግሞ፥ ቁልፉን የያዘው ሰንሰለት እያየነው በአየር ላይ ተንሳፈፈና በመካከላችን ወደቀ። የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ፣ ቸርነቱና ፍቅሩ፣ የሰማዕቱም ፍቅር ከምናስ በው በላይ ሆነብን። ይህ ሁኔታ፥ በአንድ ወቅት እናቴ የጠፋባትን የአንገት ሐብል፣ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንዴት እንደመለሰላት አስታወሰኝ።[7]

<u>ሰማዕቱ አቡ ሰይፈን</u>፦ መስከረም ፲፮ ቀን ፲፱፻፶ ዓ.ም.፥ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ፣ እማሆይ ኬርያ እስክንድርን የቅ.ጊ.ሴ.ገ. እመምኔት አድርጎ ሾማት። ሥርዓቱን የፈጸሙላት፥ የኋላው የኅል-ሶርያን ገዳም ጎላፊ (፲፱፻፵፭-፲፱፻፹፪) ብፁዕ አባ ቴዎፍሎ ስና የኋላው የቤሊና ሊ.ጳ. ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ (፲፱፻፵፭-፲፱፷፫) ናቸው። በብፁዕ ወቅ ዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ዘመነ ፕትርክና ከተሾሙት እመምኔቶች፥ እማሆይ ኬርያ ቀዳሚዋ ናት። በእማሆይ ኬርያ ሲመት ምክንያት፥ ከኃላፊነት የተገላገልሁና ደመለ ጥሁ መሰለኝ። በተቻለኝም ከእንዲህ ዐይነት ነገሮች ለመራቅ ጥረት አድርጌያለሁ። እንዲሁም፥ በገዳማችን ጎላፊነት መረከብ የሚችሉ፥ ብዙ ጠንካሮችና ብቁዓን መነኮሳ ይያት ስላሉና፤ እኔ ከሁሉም በዕድሜ የመጨረሻ ትንሿ በመሆኔ ምክንያት፥ የአቡ

[7] {ከፍል ሁለት ምዕራፍ ፩ ገጽ ፻፸፭ን ይመልከቱ።}

እማሆይ፥ ፈገግ አለችና «አግዚአብሔር ከእኔ ቀጥሎ ጎላፊነቱን የሚረከበውን ሰው ይገልጥልኝ ዘንድ እየጸለይሁ ነበር። እናም አሁን አንቺ ወደዚህ ከመምጣትሽ በፊት፣ አንቺ ያየሽውን ራሄይ አየሁ ስትለኝ እማሆይ ምን ማለት ነው? ትርጕሙ ምንድር ነው? አልኋት። አየሳቀችብኝ «ሦስቱ አረጋውያኑ አባ እንጦንስ፣ ሊቀ ካህ ናት አባ ሺኑዋና አባ ቋኵሚየስ ናቸው። ራሔይም ከእኔ በኋላ አንቺ ጎላፊነቱን እንደ ምትቀበዪ የሚጠቁም ነው። ከዕረፍቴ በፊት ብትረከቢኝና ብታስደስቺኝ ብዬ እመኖ ለሁ አለችኝ። እኔ ሐሳቧን አልተቀበልሁትምና ክርክር ቀጠልን፦

- እናቴ፥ እንዲህ ያለ ነገር ስትናገሪ ለመሆኑ ትወጂኖለሽ?
  - ✓ በጣም አወድሻለሁ።
- ለይ ብትወጂኝማ፥ አሁን ያልሽውን ነገር ባልተናገርሽ ነበር።
  - ✓ ለምን?
- ምክንያቱም፥ በኃላፊነቱ መከራ ውስጥ አልፈሻልና።
  - ✓ በእርግጥም በብዙ መከራ ማለፌን አልክድሽም።
- እና ታድያ፥ እንዴት ወደዚህ መከራ እንድገባ ትመኚልኖለሽ?
  - ✓ ልደ! ይሄ የሚሆነውኮ ስለ ገዳሙ ደኅንነት ሲባል ነው።

እማሆይ ኬርያ ከዕረፍቷ በፊት ጎላፊነቷን ለማስረከብ በጣም ፈልጋለች። ደስ ተኛ እንድትሆንና በእኔም ልትኮራብኝ እንደምትፈልግም በአጽንኦት ነገረችኝ። እንዲ ሁም ስለ ገዳሙ ደኅንነት እርግጠኛ መሆን ትፈልጋለች። በመጨረሻ፥ በዚህ ጉዳይ ለእኔ ልታዝኚልኝ ይገባሽ ነበር። አንቺ ግን ደስተኛ ነኝ ትያለሽ ብያት አምርሬ አለቀ ሰሁ። አታልቅሺ፥ ይህ አሁን የተነጋገርንበት ጉዳይ «ያየሽው ራሄይ ትርጕም ነው፣ አንቺም ጎላፊነቱን ተቀብለሽ ታገለግያለሽ! ይኸው ነው በቃ!» አለችኝ።

<u>ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስና፥ የገዳሙ ቁልፍ</u>፦ ከጊዜያት በኋላ፥ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄር ሎስ ፮ኛ፣ በአርጌዋ ካይሮ ለሚገኘው የሰ.ቅ.ጊ.ሴ.ገ. እመምኔት ለመሾም ስለ ፈለጉ፥ ለጣማፍ ኄራኒ ስልክ ደውሎ፣ እርሷን ሊሾማት ማሰቡን ነገራት። ፈቃደኛ ባለመ ሆኗ፥ «አዲስ እመምኔት እስኪሾም ድረስ፣ እርሷ በኃላፊነት እንድታስተዳድር ስለ ጠየቃት፥ በየቀኑ በጠዋት ተነሥታ ወደዚያ ትሄዳለች። እዚያ ስታገለግል ትውልና ማታ ወደ በላቷ ትመለሳለች። በዚህ ጊዜያዊ አገልግሎት፥ እማሆይ ኬርያ እስክንድር አብራት ትመላለስ ነበር። በዚህ ጎላፊነቷ የገጠማትንም ነግራናለች፦

በየቀኑ እንግዶችን ተቀብዬ አስተናግዳለሁ። ወደ ሰማዕቱ መካነ ዐፅም እየወሰ ድሁ አስገኛለሁ። የገዳሙን ወጪና ገቢ ተቆጣጥሬ በመዘገብ ላይ አሰፍራለሁ። ስለዚህ ከባድ ውጥረት ላይ እንዳለሁ ይሰማኝ ነበር። አንድ ቀን፥ ከውሰጤ በጣም ጥልቅ በሆነ ሰሜት «ቅዱስ ጊዮርጊስ! እንደማልወድህ እነግርሃለሁ፣ አንተን አልፈለ ግህም፣ ገዳምህንም አልፈልግም» ብዬ በምሬት ተናገርሁ። ወዲያውኑ በሚደንቅ

ሰይፊን ገዳም እመምኔት ያደርጉኛል ብዬ መቼም መች አስቤው አላውቅም። ስለዚህ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም ኀላፊነት ካመለጥሁ፤ ከዚህም ማምለጥ እንደምችል ታሰበኝ።

ሆኖም፥ ገና እመምኔታችን በሕይወት ሳለች፤ አቡ ሰይፊንን በሕልሜ አየሁት። እንዲህም አለኝ፦ «አድምጪኝ! ገዳሜን ከአንቺ ሌላ ማንም እንዲያስተዳድርልኝ አል ሻም። እኔ ከሁሉም ታናሽ ነኝ የሚል ምክንያት ብታቀርቢም፥ ያለ አንቺ አልፈል ግም። አሁንም ወደ አንቺ የመጣሁት፥ ይህ ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን ልነግርሽ ነው። የእኔም ፈቃድ ይኸው ነው» አለኝ። ከዚያ ቁልፎቹን ሁሉ፥ ከእማሆይ ኢላርያ እና ከሌሎችም በኃላፊነት ከነበሩ መነኰሳይያት ሁሉ ተቀበለና፥ በኣንድ ላይ አስሮ ወደ እኔ ሊወረውረው ሲል፥ ለማምለጥ እንደ መሮጥ አልሁ። ሆኖም፥ ቁልፎቹን በኣንገቴ አጠለቃቸው። ምን ላርጋቸው? ስለው፥ የገዳሜ ቁልፎች ናቸው። ከኣንቺ በቀር ማንም እንዲይዛቸውም ሆነ ገዳሜን እንዲመራ አልሻም አለ። ይህ ሊሆን አይ ችልም! ይህ የእኔ ጉዳይ አይደለም፥ ብዬ ቁልፎቹን ከኣንገቴ አውልቄ ወደ እርሱ ወረ ወርኋቸውና አልፈልጋቸውም ስለው፥ አሁንም መልሶ በኣንገቴ አጠለቀው። ወደ ራሱ ሳበኝና «ከኣንቺ ሌላ ማንም አይሆንም፤ ደግሜ እልሻለሁ፥ ከኣንቺ ሌላ ማንም አይሆ ንም» አለኝ። ይህን ሕልሜን ምሥጢር አድርጌ ያዝሁት፥ ለኣበ ንስሓዬም ሆነ ለእ መምኔቷ አልነገርኋቸውም። ምክንያቱም እማሆይ ኬርያ፥ እንኳን ይህን ሰምታ ይቅ ርና፤ ጥንቱንም ሳትሞት በፊት ኀላፊነቱን ተረክቤ ማየት ትሻለችና ነው።

እማሆይ ኬርያ እስክንድር፥ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም በተሾመች በዓመቱ፤ እማ ሆይ ኬርያ ዋስፍ አረፈች። የቤሊናው አቡነ ቄርሎስ፥ ጸሎተ ፍትሓት ሊያደርስ ሲመጣ፤ እግረ መንገዱን ከኣቡነ ቄርሎስ ፪ኛ ተቀብሎ ያመጣውን የሹመት ደብዳቤ አሳየኝ። እኔ ግን አልቀበልም ብዬ አለቀስሁ። እርሱም «እውነት አላት! ልጅ ነችኮ። እንዴት ትንሽ ልጅ ለኣስተዳዳሪነት ይሾማል? ይህ ምንም ዐይነት ስሜት አይሰጥም። ፖፕ ቄርሎስ ምን ነክቶታል? ምንም እንኳን በጎ፤ ብልኀና የተቀደሰ አባት ቢሆንም አሁን ግን ስሕተት ፈጽሟል»። ካለ በኋላ፥ «ልጀ! አድምጪኝ፤ ደብዳቤውን ያለ ምንም ተቃውሞ ተቀበይኝ። ምክንያቱም የተላከው ከብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ነውና፤ እንቢ አለች ብሎ ወደ እርሱ መመለስ ነውር ነው። ባይሆን በኣካል ሄደሽ አነጋግሪው» አለኝ።

ይህ ሊሆን የማይችል ነገር ነው፤ ብዬ ማልቀሴን ቀጠልሁ። ልክ ነሽ ልጀ! እንዲህ ዐይነት ትእዛዝ አይሠራም፤ አንቺ ገና ብዙ ይቀርሻል አለኝ። እማሆይ ኢላ ርያ ደግሞ፥ ፍጹም ትሕትና በተሞላው ሁኔታ፥ ወደ እኔ መጣችና፤ ትከሻዬን መታ እያደረገች ግንባሬን ስማ «ማልቀስሽን አቁሚና ደብዳቤውን ተቀበዪ፤ የብፁዕ ወቅዱስ አባታችንን ትእዛዝም እሺ በይ፤ ማናቸውንም ከባድ የሆኑትን ሥራዎች እኛ እንሠ ራልሻለን፤ ቀላል የሆነውን ብቻ ለኣንቺ እንተዋለን» አለችኝ።

እኔ አሁንም በእንቢታዬ ጸንቼ፥ «እንዴት ሊሆን ይችላል? የማይሆን ነገርኮ ነው» ብዬ ብከራከርም እነርሱም አይዞሽ አትጨነቂ በማለት ኮማሪጋጋት ወደኋላ አላሉም። ወላጅ አባቴ ይህን ጉዳይ ሲሰማ፥ «እሺ እንዳትያቸው፤ የገዳሙን ኀላፊነት ከተቀበልሽ አንቺ ልጄ አይደለሽም። እኔም አባትሽ አይደለሁም። ጠፍተሽ ቶሎ ወደ ቤት ነይ። እኔ እደብቅሻለሁ፤ ሌላ ሰው እስኪሾሙ ድረስም፥ የት እንዳለች አላውቅም እያልሁ አቆይሽና፥ ሁሉም ነገር ከተስተካከለ በኋላ፥ ተመልሰሽ ትሄጃለሽ» የሚል ደብዳቤ ላከልኝ።

ማልቀሴን ማቆም አልቻልሁም። ወደ መንበረ ፓትርያርክ ሄድሁና፤ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛን «ብፁዕነትዎ እንዴት ነው እሱ? እኔ ለዚህ ሥራ ብቁ አይደለሁም። እርስዎም ቢሆኑኮ ስለ እኔ ምንም አያውቁም። የንስሐ አባቴም አልነበሩም። አንድ ቀን ብቻ ነው ለራስ ምታቴ የጸለዩልኝ»። ስለው «እሺ! እንግድያው ለዚህ ኀላፊነት ማን ይመጥናል ብለሽ ታሰቢያለሽ?» አለኝ። «እማሆይ ኢላርያ ለዚህ ሥራ ተገቢ ነች። በዕድሜ፤ በቅድስና፤ በጸጋ፤ በጥበብ ሁሉ ሹመቱ ይገባታል። በዚያ ላይ ምክ ትል አስተዳዳሪ ነበረች። የሌሎቹም ምርጫም እርሷ ናት። እማሆይ ፌቢም ብትሆን ለዚህ አታንስም» አልሁት።[8]

ብፁዕ አባታችንም «አዎን ልክ ብለሻል! እማሆይ ኢላርያን ፍጹም ነበር የረሳ ኋት። ነገር ግን፥ ይህ በእኔና በኣንቺ ብቻ መቅረት ያለበት ምሥጢር ነውና፥ እስኪስ ናወን ድረስ ለማንም እንዳትነግሪ። እንደማስበው ከሆነ መነኰሳይያቱም ቢሆኑ፥ እር ሷን ይመርጣሉ። በቃ እርሷው ናት የምትሾመው። በይ እንግዲህ አንቺም አትበ ሳጪ። ለማንም ቢሆን ይህን ምሥጢር እንዳትናገሪ። አንድ ቀን እመጣና እሾማታ ለሁ» አለኝና እኔም አመሰግኜውና መልካሙን ተመኝቼለት ተመለስሁ። የፓትርያር ኩን ቃል አምኜ ተቀበልሁ እንጂ፥ ሊያረጋጋንና ሊያሞኝኝ እንዳሰበ በፍጹም አልተረ ዳሁም። ደስ እያለኝ ወደ በኣቴ ተመለስሁ። ለካስ ጠፍቼ ወደ አባቴ ለመሄድ እንዳሰ ብሁ እማሆይ ኬርያ እስክንድር ነግራው ኖሯል፤ ሊያረጋጋንና በብልሓት ሊይዘኝ የወሰነው። ከእርሱ ዘንድ ስመለስ፥ የነበረኝን መረጋጋት ያዩ እኅቶች ደግሞ፤ እየተገ ረሙ ያ ሁሉ ለቅሶና ኀዘን የት ደረሰና በሰላም ተተካ? አሉኝ። እኔም አባታችን ጸል ዮልኝ ነው ብዬ መለስሁላቸው። እንዳትናገሪ ያለኝን ምሥጢር ግን አልተናገርሁም።

ቡረኩ ሲመት፦ ጥቅምት ፭ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ለኛ ጠዋት፤ በኣሮጌው የኣቡ ሰይፊን ቤተ ክርስቲያን፤ የነግህ ጸሎት አድርሰን እንደ ወጣን፥ ወደ በኣታችን ስንመለስ፥ የዚ ያን ጊዜ የገዳማችን አበ ነፍስ የነበረው፥ አባ ጳውሎስ አል-ባራሙሲን (የኋላው ብፁዕ አባ ማርቆስ የቃና ሊ.ጳ. ፲፱፻፶፭-፲፱፻፺፬) አገኘነው። እርሱም፥ ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን

[8] እማሆይ ፌቢ (Feeby/Phoebe) በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. ወደ ገዳም ገብታ፥ በባሕታዊው አባ ሚና አል-ባራ ሙሲ እጅ ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. መነኰሰች።

ዛሬ እዚህ መጥቼ እቀድሳለሁ ብሏል። ለነጋ የቀመስሽው ነገር አለንዴ? ሲለኝ ገና ከጸሎት መውጣታችን ነውና ማንም የቀመሰ የለም አልሁት። እርሱም መልካም አንግዲህ አስቀድሳችሁ ትቁርባላችሁ አለ።

እንግዲያው ልተጣጠብና ልብስ ቀይሬ ልምጣ፤ ብዬው ልሄድ ስል፥ ልብሰሽን መነኰሳይያቱ ያዚጋዱልሻል አለኝ። ደንግጬ የምን ልብስ? ምን እየተደረገ ነው? ስለው፤ ምን እያልሽ ነው? ምን ተደረገ? ብሎ መልሶ ጠየቀኝ። በውስጤ ጥርጣሬ ስለ ሰፈኑ አባቴ! እንዴት እንዲህ ያደርጋሉ? ስለው፥ ለእጎቶችሽ መነኰሳይያት እን ኳን በማትናገሪው መንገድ (በቁጣ)፤ እኔን እንዴት ታናግሪናለሽ? አለኝ። «ራሴን መቆጣጠር ስላልቻልሁ ነው፤ ይቅርታ ያድርጉልኝ» አልሁት። አሁን ቁርጤን ስላወ ቅሁ፥ ልቅሶዬን ጀመርሁ። እርሱም ልብሷን አምጡላት ብሎ አዘዘ።

ከዚያ በሁለት እጆቹ ይዞ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ለማስገባት ሲጎትተኝ፤ መነኰሳይያቱ ደግሞ፥ እንደሚታረድ ከብት ከኋላ እየገፉኝ ያግዙት ነበር። መቅደስ ከገባን በኋላ፥ እኔ አለቅሳለሁ፤ መነኰሳይያቱም ዙሪያዬን ከበው ያዩኛል። የቀብር ሥርዓት የሚፈጸም ነበር የመሰለው። የሚቀብሩት ደግሞ እኔን ነው። ይህን ትዕይንት ሲከ ታተል የነበረውና፤ በፓትርያርኩ ተጋብዞ የመጣው የሱዳን ሊ.ጳ.ብ. አባ ዮሐንስም (፲፱፻፯-፲፱፻፰) እኔን እያየ ያለቅሳል። አበ ንስሓዬ፥ ምንም ነገር የመናገርም ሆነ የመ ጠየቅ ዕድል ሳይሰጠኝ ሥርዓቱን ጀመረ። ጎብስቱንና ወይኑን የላከው አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ራሱ ሲሆን፥ የግል አስኬማውንም ያጠልቁልኝ ዘንድ ልኳል።

የዕለቱ ምንባብም ስለ መልካም አረኝነት የሚናገረው፤ ፓትርያርክ ሲሾም የሚነበበው፥ የዮሐንስ ወንጌል ፲፭-፲፮ መሆኑ ሥርዓቱን ልዩ አድርጎታል። እኔም እያነባሁ እግዚአብሔር እንዲጠብቀኝ፣ እንዲያበረታኝና ቀናውን መንገድ እንዲመራኝ ጸለይሁ። «እኔ ግን ዘወትር ከአንተ ጋር ነኝ፤ ቀኝ እጅንም ያዝኸኝ። በአንተ ምክር መራኸኝ፤ ከክ ብር ጋር ተቀበልኸኝ። . . . ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል፤ መታመኛዬም እግዚ አብሔር ነው፤ በጽዮን ልጅ በሮች ምስጋናህን ሁሉ እናገር ዘንድ» (መዝ.፸፫፥፳፰፤ ፸፬፥፩)። ብዬ ጸለይሁ። «መልካም አረኖ አኔ ነኝ። መልካም አረኖ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል። መልካም አረኖ እኔ ነኝ። አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ» እንዲል ወንጌለ ዮሐንስ (፲፥፲፭፤ ፲፬-፲፮)።

ከተሾምሁ በኋላ ወደ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ሄጄ፥ ወቀሳዬን በትሑት አንደበት አቀረብሁ። «አሁን ምንድር ነው የሚደርገው? ብፁዕነትዎ። አስኬማ መልበስ ማለት፥ ሙሉውን ዳዊት በቀን ሁለት ጊዜ መድገም፤ ዝማሬ ማቅረብ፤ እስከ ሰባት መቶ የሚደርስ ስግደት መስገድ ይጠይቃል። የአስኬማውን ግዴታና የኃላፊነቱን ሥራ በአ ንድነት እንዴት ማስሄድ ይቻለኛል?» ስለው፥ ዳዊቱንና መዝሙራቱን ወዲያና ወዲህ ባልሽ ቊጥር በቃልሽ ድገሚ አለኝ። በእኔ ላይ ስላደረጉት ነገር ደስተኛ ነዎት ማለት

ነው? ስለው «ልጀ! በዚህ ጉዳይ ላይ አብዝቼ ጸልዬበታለሁ። የተረዳሁትም ይህ ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን ብቻ ነው። ታድያ ሌላ ምን አማራጭ አለኝ? ከፈቃ ዱስ ወዴት እሄዳለሁ? ብሎ መለሰልኝ።

ጣማፍ ጌራኒ ሹመቷን ከተቀበለች በኋላ፥ ወዲያው ነበር ሥርዓተ ገዳሙን እንዳለ የቀየረችው። እግዚአብሔር ትክክለኛውን ሥርዓተ ገዳም ይገልጽላት ዘንድ አብዝታ ትጸልይ ነበር። ምክንያቷንም እንዲህ ስትል ገልጣልናለች፦

በመነኰሳይያት መካከል ያለው መለያየት በእጅጉ የሚያቆስለኝ ችግር ነበር። ድሃዋ መነኰሲት ያጣች የነጣች ሆና ስትኖር፤ ባለ ሀብቷ መነኰሲት ደግሞ፥ የፈለገ ችውን እያገኘች እንደ ልቧ ትኖራለች። ሥራ ሠርታ ገንዘብ ማግኘት የምትችለው፤ ወይም ከቤተሰብ እርዳታ የሚደረግላት፥ ያለ ችግር ስትኖር፤ ዘመድ የሌላትና ለመ ሥራትም ዐቅምና ጤና የሌላት ግን፥ በድኽነት እየታሸች ትኖራለች። በላቶቻቸውም በዚያው ልክ ይለያያሉ። ሀብታሟ በበላቷ ብዙ ቊላቊስ ሲናሯት፤ ድሃዋ ግን ምንም ነገር የላትም። ይህ በእርግጥም (በተለይ በገዳም ውስጥ ሲከሰት) የሚያሳምም ሥር ዓት ነው። ስለዚህ የእያንዳንዷ መነኰሲት በላት አንድ ዐይነት፤ እንዲሁም የውስጥ ይዘቱ ፍጹም ተመሳሳይ እንዲሆን ለማድረግ ወሰንሁ። በዚህ ሁኔታ፥ ስለ ንብረቷ ወይም ስለ ድህነቷ የምትጨነቅ መነኰሲት እንዳትኖር ማድረግ ይቻላል። ስለዚህ የሁሉም መነኰሳይያት ትኩረት ወደ ጸሎታቸው፤ መንፈሳዊ ሕይወታቸው፤ የጋራ ጉባ ፊነታቸውና ድኅነተ ነፍሳቸው ብቻ ይሆናል።

በቀደመው ሥርዓት፥ ታላላቅ ነጋዴዎችና ሱቅ በደረቴዎች ወደ ገዳሙ እየ መጡ ንግድ ይለዋወጡ ነበር። ጣማፍ ጌራኒ፥ ወዲያው እንደ ተሾመች የመጀመሪያ ሥራዋ፤ ይህን ማስቆም ነበር። በፊት በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ይጸለይ የነበረውን የጋራ ጸሎት፤ አሁን በቀን ሦስት ጊዜ እንዲጸለይ አደረገች። ይኸውም የሰርክ፣ የሌሊትና የነግህ ጸሎት ነው። ከጊዜያት በኋላ፥ ከአረጋውያኑ መነኰሳይያት አንዷ፤ ከዕረፍቷ ጥቂት ቀደም ብላ፥ የማኅበራዊውን ሕይወት ጥቅምና ጣማፍ ጌራኒ ይህን ለውጥ ለማ ምጣት፤ ያሳለፈችውን ውጣ ውረድና እነርሱም ያደርሱባት የነበረውን ፈተና በጸጸት መስክራለች። ጣማፍንም «እናቴ! ሁላችንም በድለንሻልና ይቅርታ አድርጊልን። ስንት ጊዜ ነው መመሪያሽን አንቀበልም፤ በአንቺ መንገድ አንሄድም፤ በአንድነት ሕጉም አንመራም ብለን ፈተናሽን ያከበድንብሽ? አንቺ ግን፥ በትዕግሥትሽ፤ በፍቅርሽ ብዛ ትና ጎይል፥ ሁሉን ተቋቊመሽ፤ እኛንም ማረክሽን» ብላታለች።

በሦስቱ የጸሎት ጊዜያት፥ በንቃትና በቅንነት መጥተው ለሚጸልዩት፤ ምን ያህል ሰማያዊ ዋጋ እንደ ነበረው ጣማፍ ትነግረን ነበር፦ ወላዲተ አምላክ ሁል ጊዜ ኣየተገኝች ጉባኤውን ትባርካለች። በየዕለቱ ከበላቷ ደስ ብሏት፤ ለጸሎት ለምትመጣ መነኰሲት ሁሉ፤ የሚበራ ፋናስ ትሰጣለች። ደስ ሳይላት፥ በማጉረምረምና እንዲ

ያው ሕጉን ለማክበር ብቻ ብላ ለምትመጣው ደግሞ፤ የማይበራ ፋናስ ትሰጣለች። እንግዲህ በስንፍና ወይም አንድነቱን ባለመደገፍ፤ ቄራሽ ከበላኋቷ የማትወጣዋማ ያጣችውን በረከት ማወቅ አያቅትም። የበራም ሆነ ያልበራ ፋናስ አታገኝም። ስለዚህ ያለማቋረጥና በትጋት ለሚመጡት እጎቶች፤ እመቤታችን መጽናኛ ሆናቸዋለች።

ታኅሣሥ አንድ ቀን፥ በአ.ሰ.ቤ.ክ. ተሰባስበን ስንጸልይ፥ መቅደሱ ልዩ በሆነ የዕጣን መዓዛ እንደታወደ እኛም ምስክሮች ሆነናል። ደስታችንም ገደብ አልነበረውም። ጣማፍ ደግሞ፥ ወላዲተ አምላክ በግድግዳው ላይ ከነበረው ሥዕሏ ወጥታ ታየችኝ። አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ (፲፰፰፫-፲፱፵) እና አባ አብርሃም ዘፈዩም (መፍቀሬ ነዳይ) ጽንሓሕ ይዘው አብረዋት ነበሩ። ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ገብተው፥ መንበሩን ሦስት ጊዜ ከዞሩት በኋላ፥ በእያንዳንዷ መነኵሲት አጠገብ እየባረኩ አልፈዋል። ከፊት እመቤታችን፤ ከዚያ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ፤ ከዚያ አባ አብርሃም ዘፈዩም ሆነው ከባረኩ በኋላ፥ ተመልሰው ወደ መንበሩ ሄደው ተሰወሩ። በዚህ ጊዜ የነበሩት መነኵሳይያት ሁሉ የቡራኬው ተሳታፊ በመሆናቸው ተደስተዋል። የራስ ወይም የሆድ ሕመም ይሰማቸው የነበሩትም ፈውስ አግኝተዋል አለችን።

ይህ የሌሊትና የነግህ ሥርዓተ ጸሎት፤ የሚያስገኘው በረከትና የመንፈስ ሰላም፤ የጠላት ዲያብሎስን ንዴት ቀስቅሷል። በታኅሣሥ ወር በዕለተ ሰንበተ ክርስቲያን፤ የመጀመሪያው የማኅበሩ ጉባኤ ላይ፥ ዳዊት እየተደገመ፤ ማዕጠንት ሲታጠን፥ ሁላችንም በተመስጠ ሥርዓቱን እየተከታተልን ሳለን፥ ከቤተ ክርስቲያኑ በር አካባቢ፤ አስከፊ የሆነ የእንስሳ ጩኸት በድንገት ሰማን። ስንወጣ ግን ምንም ነገር አልነበረም። ይህ ሥርዓተ ጸሎቱን ለመረበሽና እኛን ለማደናገጥ ያደረገው የመጀመሪያ ሙከራው ነበር። ይህ የሚገልጽልን የጣማፍ ጌራኒን ጥልቅ መንፈሳዊነት ነው። በእርሷ ጥረት ባስያዘችን ሥርዓት፥ በመዝሙርና በጸሎት ስለተገኘው በረከት ወደፊት እናያለን።

የአንድነት ኑሮውን ለመመሥረትና፤ ደቀ መዛሙርቷ በተገቢው ሁሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ፥ ከምታደርገው ጥረት በተጨማሪ፥ በገዳሙ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን መኖር አለበት የሚል አዲስ ሐሳብ ይዛ ተነሣች። ይህን ለማድረግ ያሳሰባትና፥ አረጋውያኑና ዐቅመ ደካሞቹ፥ ብዙ ሳይጉላሉ አስቀድሰው ለመቊረብ ይችሉ ዘንድ ነው። በተሾመች በሁለተኛ ዓመቷ፥ ግንባታውን ጀምራ ከአንድ በላይ መንበር ያለው ቤተ ክርስቲያን አሳነፀች። አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ገና ከፐትርክናው በፊት የተናገረው ትንቢትም ተፈጸመ። ልጆቿ በመንፈስ ያደጉ ይሆኑ ዘንድ፥ በጽኑ ስለምትሻ፤ ገድላትና የቤተ ክርስቲያን ታሪክችን ያለ ማስታጎል ታነብላቸዋለች። እንዲያነቡም አመቺ ሁኔታን አዘጋጅታላቸዋለች። ይህ እንቅስቃሴዋ ደግሞ፥ ገዳሙ አንድ ልዩ ቤተ መጻሕፍት ያስፈልገዋል የሚል ጥያቄ ይዞ መጣ።

መንፈሳዊት እናታችን ጣማፍ፥ በዚህ ሁኔታ ቀኖና ጳኩሚየስን እያነበበችና ከራሷም ከእኛም ሕይወት ጋር፤ እያናበበች ልምምድ በምታደርግበት ጊዜ፥ የእያንዳንዳችን ዐቅም ከሚፈቅድልንና ከችሎታችን በላይ የሆነ፤ ምንም ነገር እንድናደርግ ጠይቃን አታውቅም። ፍቅሯ ግን ለሁሉም የሚቸር እንጂ፥ አንዱን ከሌላው የምታለይበት አይደለም፤ አታዳላምም። ልዩነት ወይም አድልኦ ካደረገችም ለደካሞቹና ለሕሙማኑ ብቻ ነው። እነርሱ ልዩ ጥንቃቄ ያሻቸዋልና።

እንደ እናት፤ አለቃ፤ አስተማሪና መንፈሳዊት መሪ፤ ልጆቿን እያስተዳደረች፥ በእግዚአብሔር መንገድ ስትጓዝ፥ በትሕትና፤ ብዙ መከራ በመቀበል፤ ፈተናዎችን ሁሉ በመቋቋምና በትዕግሥት ነው። ለእያንዳንዷ እጎት ጎላፊነቷን እንድትወጣ ትእዛዝ ስትሰጥ፥ ያለ ምንም ተጽእኖና አስገዳጅነት ነው። በእምነቷ ጽናትና በጥልቅ መንፈሳዊነቷ ምክንያት፥ ያለመችው የአንድነት ኑሮ ማኅበር፤ በብዙ ፈተናዎች ውስጥም ቢሆን፥ የተሳካ እንደሚሆንና የገዳሙ ማኅበራዊ ሕይወት ለምልሞ፤ አብቦና አፍርቶ እንደምታይ እርግጠኛ ነበረች። የደናግል መነኵሳይያቱ መንፈሳዊ ሕይወት፤ እጅግ የላቀ እንዲሆን፥ ሌት ከቀን ያለ ዕረፍት በመሥራት፤ ለዘለዓለም የማይጠፋና እየሰፋ የሚሄድ ተግባር ፈጽማለች። የእምነቷ ጽናት፤ የዓላማዋ ቀናነትና ዐላማዋን ለማሳካት ያላት አልበገር ባይነት፤ የዘመኑ ታላቅ መሪ እናት አድርጓታል። ይህ አርኣያነቷ ብዙዎችንም ወደ በረኻ እስከ መመነን አድርሷቸዋል።

ትመክራለች፤ ታጽናናለች፤ ታበረታለች፤ ትሰብክለች፤ ጎይለ መንፈስ ቅዱስን ታሳድራለች። ለእያንዳንዷ መነኵሲት የምትሰነዝረው ቃል ተገቢውን ቦታ የሚመጥንና የተመዘነ ነው። ብስጭት፤ ድብርት ወይም ጥርጣሬ፤ በኣጠገቧ እንዲያልፉ አትፈቅድላቸውም። የመንፈስ ልጆቿን ስትመክርም፤ ሰማያዊው መንግሥት፥ በወርቅና በብር ብዛት አይገዛም፤ መንግሥተ ሰማይን ለመውረስ የሚቻለው፥ ራስን በማዋረድ፤ ልብን ንጹሕ በማድረግ፤ ሁሉን በእውነትና ያለ ልዩነት በመውደድ፤ በማንኛውም ነገር ባለማዳላትና የበላይ ሆኖ ባለመታየት ነው። የነፍሱን ድኅነት የሚሻ ሁሉ፤ የክብር ባለቤት የሆነ አምላክ ያስተማረንን ትምህርት አጥብቆ ይያዝ፥ ትላለች።

እያንዳንዱ እንቅስቃሴዋ፤ ትምህርቷና ምክሯ ድንቅና ደስ የሚያሰኝ በመሆኑ፤ ከእርስዋ ጋር ስንሆን፥ ከሰው ጋር ሳይሆን ከመላእክት ጋር፥ በሰማያት አንጻር ያለን ሆኖ ይሰማናል። ያለማቋረት የምታየውንና ሁሌም አብራው ያለችውን እግዚአብሔርን እናይ ዘንድ፥ የክብረ መንግሥቱን መስኮት በትንሹ ከፍታ፥ የብርሃኑን ጭላንጭል የምታሳየንም ይመስለናል። ማለቂያ የሌለው የፍቅር ምንጭ ናትና። ቀኖና ጳኩሚየስን ለመመሥረት፤ ልጆቿን በመንፈስ ለማሳደግና ገዳሙን በስፋት ለማደራጀት፤ በምትፈጽመው ገድል ሁሉ፥ የስኬቷ ምሥጢር ረድኤተ መለኮት ብቻ ነው። አንድ ጥያቄ ይዛ፥ ወደ ፈጣሪዋ በጸሎት ስትቀርብ፥ የጥያቄዋን ይሁንታ እዚያው ታገኛለች። በበላኋቷ ግድግዳ ላይ ካለው፤ የእመአምላክ ሥዕለ አድኅኖ ላይ፥ ብርሃን ይፈነጥቃል።

ጥቅና በኣቷን ይሞላዋል። ከዚያ እመቤታችን በፈገግታ ወደ እርሷ ትቀርብና በብርሃ
ናዊ መስቀል ትባርካታለች፤ «የምወደው ልጅ ሞገስ ሆኖሻል። በሥራሽ ሁሌም
ውጤታማ . . . ውጤታማ . . . ውጤታማ . . . ብቻ ትሆኖለሽ» ትላታለች።

በዚህ በረከት፥ ሰማያዊ መጽናናት ታገኛለች፤ እያንዳንዱ እርምጃዋ ይባረክላ
ታል። ስለ እኛ ሲል፥ በመስቀል ተሰቅሎ የሞተውን የጌታችንን ፍቅር፤ ያለ ልክ ያለ
ገደብ የሚያድለንንና ስለ እኛ ድኅነት ሲል እስከ መስቀል ሞት ድረስ ያደረሰው
ጎያል ፍቅሩ፥ ይታያታል፤ ይሰማታል፤ ትኖረዋለች። ምንም እንኳን፥ ለዚህ ፍቅሩ
ውለታውን በፍቅር ለመክፈል ዐቅሟ የሚፈቅድላት፤ የቸርነት ነጸብራቁን ኢምንት
ጨረፍታ ያህል ብቻ ቢሆንም፥ ከግልጽነቷና ከፍቅሯ ጽናት የተነሣ፥ ስለ ፈጣሪዋ
ክብር ስትል ሰማዕት ለመሆን የሁል ጊዜ ምኞቷ ነበር። በየጸሎቷ መካከል፥ ለሰማዕ
ትነት ክብር እንዲያበቃት ታሳስባለች። ያንን ሁሉ የበሽታ ዐይነት ተሸክማ እየተሰቃ
የች እንኳን፥ የሰማዕትነት ጥያቄዋ አይቋረጥም።

የኣቡ ሰይፊን የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያኑ፤ ቅዳሴ ቤት በከበረበት ኒሓሴ ፩
ቀን፤ ግብፅ ውስጥ ታላቅ በዓል ይደረጋል። አንዱ በዓል፥ በ፲፱፻፫ ዓ.ም. ለሕክምና ወደ
ስዊዘርላንድ ካደረገችው ጉዞ ጋር ስለ ገጠመባት ደስተኛ እንዳልነበረች ነግራናለች፦

ሌሊት በሓኪም ቤት ኣልጋዬ ላይ እንደተኛሁ፤ ለኣቡ ሰይፊን ዝማሬ እያቀረ
ብሁና እየጸለይሁ ነበር። ኣቡ ሰይፊን ተገለጠልኝና እንዲህ አለኝ፥ «በሽተኛ የሆንሽው
በፈቃደ እግዚኣብሔር ነው። ይህ ለኣንቺ የተፈቀደ መከራ መስቀል ነውና ትከብረበ
ታለሽ። የእነዚህን በሽታዎች ሕመም መቋቋም፥ ከሰማዕትነት እኩል ነው። ኣምላክ ስለ
እርሱ ስም ሰማዕት እንዲያደርግሽ ትጸልዩ የለምን? ኣሁን ሰማዕትነትሽን እየተቀበልሽ
ነው ያለሽው። እኔም እጸልይልሻለሁ። እግዚኣብሔር ከኣንቺ ጋር ይሁን» አለኝ።

ሰማዕቱ ኣቡ ሰይፊን፥ ከኣንድ ጊዜ በላይ ተገልጠላት፤ ሕመሟ የሰማዕትነት
ኣቻ መሆኑን ነግሯታል። እግዚኣብሔርም ብርታትና መረጋጋትን ይሰጣታል። ትዕግ
ሥትና ምስጋና ራሱ የሰማዕትነት ያህል ነው፤ በዚያ ላይ እርሷ በሽታዎቿን ሁሉ
በጸጋ ተቀብላ እግዚኣብሔርን ታመሰግንበታለችና። የዚህ ዐይነት ሰማያዊ ተስፋና
ቃል ኪዳን በየጊዜው ተቀብላለች። እመብርሃንም አንድ ጊዜ እንዲህ ብላታለች፦

«ሰማዕት ለመሆን ትፈልጊያለሽን?» ብላ ስትጠይቀኝ «እናቴ ቅድስት ድንግል
ማርያም! ይህ በጣም የምመኘው ክብር ነው። ነገር ግን ብርታት የሌለኝ ደካማ ፍጥ
ረት ነኝ። ኣንቺ ከኃጢ ከቆምሽልኝ እበረታለሁ። ኣንቺ ከራቅሽኝ ደግሞ መንገድ ላይ
ወድቄ እቀራለሁ» ኣልኋት። እመቤታችንም «እንግዲህ የኣንቺ ሰማዕትነት፥ በበሽታሽ
ምክንያት የሚደርስብሽ ስቃይ ነው፤ በሥራሽ የሚገጥምሽ ፈተናና የኣካልም፤ የኣእ
ምሮም ድካምሽ፥ ከሰማዕትነት እኩል ዋጋ ያለው ነው» አለችኝ።

በሌላ ጊዜ፥ ለሕክምና ከግብፅ ውጭ ነበርሁ። በመኝታ ክፍሌ ውስጥ ብቻዬን
ሳለሁ፥ ማንም የሚረብሸኝ ሰው ባለመኖሩ፥ ኢጋጣሚውን ተጠቅሜ ጸሎቴን ወደ ፈጣ
ሪዬ እያደረስሁ ነበር። ወዲያው ቤቱ በብርሃን ሞላና፥ ወላዲተ አምላክ፤ መልእክት
ልትነግረኝ ወይም ልታጽናናኝ ሳይሆን፥ አብራኝ ልትጸልይ መጣች። እርሷ በቀኜ አቡ
ሰይፊን ደግሞ በግራዬ ቆመዋል። እርሷም በይ እንጂ ጌራኒ! እንጸልይ አለችኝ። ጸሎ
ቱንም እንዲህ ስትል ራሷ ጀመረች «ልዑል እግዚኣብሔር ወልድ፥ ፈጣሪዬም ልጅም
የሆንህ፤ ኣመሰግንሃለሁ፣ ኣወድስሃለሁ፣ ኣከብርሃለሁ፣ ለክብርህም እገዛለሁ። ሥጋ
ዬን ተዋሕደህ የእናትነትን ጸጋ ያሳየሽኝ ኣሁንም ጸሎቴን ተቀበለኝ»፤ እያለች
ረዥም ጸሎት ያደረሰች ሲሆን፥ በየመኻሉ ልጅና ፈጣሪዬ ልዑል እግዚኣብሔር ሆይ!
ማለትን ትደጋግም ነበር። ልጅና ፈጣሪዬ ሆይ!»

† ቁጣህን ኣርቅልኝ፣ ይህንን ዓለም በትዕግሥትህ ኣጣኘው፣ ለፍጥረትህ የምታፈሰ
ውን ፍቅር፤ ሁሉም እንደማይቀበልህና ደስ እንደማያሰኙህም ኣውቃለሁ። ኣንተ
ግን፥ ለልጆችህ እስከ ሞት ድረስ ብዙ ኣድርገኻል።

† በኣንደበቴ ብዙ ብናገርም፣ ብዘረዝርም በተግባር ግን እንደማልፈጽመውና ውለታ
ህን እንደማልችለው ኣውቃለሁ። ቢሆንም ግን ልጅና ፈጣሪዬ ሆይ! የእጆችህ
ሥራ የሆኑትን ልጆችህን በትዕግሥት ዐይኖችህ ኢያቸው። ስለ ድክመታቸው ኣት
ፍረድባቸው። ስለ እነርሱ ቤዛነት ስትል ስለቆረስኸው ቅዱስ ሥጋህ፣ ስላፈሰስ
ኸው ክቡር ደምህ፣ በቅዱስ ደምህ ስለ ከበረው ቅዱስ መስቀልህም ይቅር በላቸው።

† በኣንተ ፍቅር የሚኖሩትን ጸጋቸውን ኣብዛላቸው። የራቁህንም በማያልቀው ፍቅ
ርህ ኣቅርባቸው። ብላ ከጸለየች በኋላ፥ ስለ ግብፅ ሕዝብ ክርስቲያን፣ ስለ ብፁዕ
ኣቡነ ሲኑዳ ሣልሳይ፣ ስለ ሊቃነ ጳጳሳቱ፣ ስለ ገዳማቱና ስለ መላው ዓለም፣ እያለ
ቀሰች በጸሎቷ ኣሳሰበች (ማለደች)። በመጨረሻም የምጠይቅህ፥ ልጅህ ጌራኒ በሰ
ማዕትነት ክብር ማለፍ ትፈልጋለች። ይህም እንደ ፈቃድህ ብቻ ይሁን። ክብርና
ምስጋና ኣስከዘለዓለም ለኣንተ ይሁን! ኣሜን።

እማሆይ ጌራኒ፥ የሰማዕትነት ክፍል የሆነውን የሕመም መስቀሏን በሓሴት
ተቀበለች። ደስታዋ እጅግ የላቀ መሆኑና ሁሉንም ስቃይዋን በትዕግሥት መቋቋም
መቻሏ፥ የበሽታዋን ጽናት ለሚያውቅ ሰው ሁሉ ያስደንቅ ነበር። መርማሪ ሐኪሞቿ
ሳይቀሩ፥ ከሕክምና ሳይንስ ዕውቀት በላይ የሆነውን፤ የበሽታዋን ብዛትና ክፉነት፥
እርሷ ከምታሳየው ሁኔታ ጋር ሊያነጻጽሩት ግራ ይገባቸዋል። የመከራን ጽዋ፥ እን
ዲህ በበሽታ ኣማካይነት እየጨለጠች፥ ወደ ውጭ ሀገር በመመላለስ ያሳለፈችው ጊዜ
የመጨረሻ የሰማዕትነት ፍላጎቷን ኣሳይቷቸዋልና።

በረድኤተ መንፈስ ቅዱስ መመሬት፦ ጣማፍ ኄራኒ ገና በወጣት ዕድሜዋ ያደረባት የእግዚአብሔር ቅዱሳን፣ የቅብጥ ቤተ ክርስቲያንና የሰማዕታቱ ፍቅር፤ በረኻውያን አባቶች የጻፏቸውን ብዙ መጻሕፍት ለማንበብ ምክንያት ሆኗታል። ለምሳሌ፦ መጽሐፈ ገነት፣ የቅዱስ ዮሐንስ ሳባ፣ የይ ስሐቅ ሶርያዊ፣ ቅዱስ ዮሐንስ «St.John Of The ladder»፣ የቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ሆሚሊስ መጻሕፍትን መጥቀስ ይቻላል።

ይህን ጥልቅ መሻቷንና የልብ ንጽሕናዋን የሚያውቅ እግዚአብሔር፤ ደብዛው ሊጠፋ የደረሰው የሴቶች ገዳም፤ ዳግም ይነሣ ዘንድ ለማደራጀቱ ሥራ እርሷን መርጦ በአ.ሰ.ሴ.ገ. አስቀመጣት። እርሷም በገዳማዊ ሕይወቷ እጅግ ደስተኛ ነበረች፥ አዘውትራ «ለምንኵሰና ሕይወት በላይ መልካምና ደስ የሚያሰኝ ነገር የለም። ለኣበውም ሆነ እማት፥ በፍቅርና ራስን በማዋረድ፣ ሕግጋተ እግዚአብሔርንም እየጠበቁና በገዳማዊ ሥርዓት እየተመሩ እንደ መኖር የመሰለና የሚወዳደረው ሕይወት የለም። ገዳማዊ ሕይወት ማለት ገነትን መሬት ላይ እንደ ማየት ነው» ትል ነበር።

በእርሷ ሕይወት ውስጥ፤ ታላቁ አባት አባ ጳላሞን ለደቀ መዝሙሩ ለኣባ ጳኩሚየስ የሰጠውን ትምህርት እናያለን። ይኸውም፦ «እግዚአብሔር ይህንን ገዳም ታላቅና ታዋቂ ታደርገው ዘንድ ሥልጣን እንደ ሰጠህ ተረድቻለሁ። እጅግ ይሰፋል፤ የመነኰሳትና መነኰሳይያት መነኻርያ ይሆናል። ብዙ ነፍሳትም ይድኑበታል። ይህንን ኀላፊነትና አብሮ የሚመጣውንም፤ እስከ የሌለው ፈተና ትቀበለው ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው»።

ለጣማፍ ኄራኒም ይህንን ኀላፊነት እግዚአብሔር በጥበቡ ሰጥቷታል። እርሷም ኀላፊነቱን በታላቅ ፍቅር ተቀብላ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራዋን ጀመረች። በኣመራር ሥራዋ ሁሉ መደገፊያዋ እምነቷ ብቻ ነበር። ከሕመሟና ከድካሟ በላይ ሆና ራሷን መልካም እርሾ አደረገች። ይህ መልካም እርሾ፤ ለሌሎች ብዙዎችም የድኅነት ምክንያት ሆነ። የኣንድነት ኑሮ ወጣኒ ለሆነው ለኣባ ጳኩሚየስ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ቃል፤ በድጋሚ በጣማፍ ኄራኒ ተፈጸመ። «አትፍራ፤ ብርታት ይኑርህ . . . የእግዚአብሔር እጅ ይመራሃል፤ ለድልም ያበቃሃልና። ወደ አንተ የመጣውን ሁሉ ተቀብለህ ከእግዚአብሔር ጋር ታገናኝ ዘንድ የእርሱ ፈቃድ ነውና»።

ምዕራፍ ሦስት።

«ዳዊትም ልጁን ሰሎሞንን፦ ጠንክር አይዞህ፥ አድርገውም፤ አምላክ እግዚአ